# ባህላዊ ስእሎች እንደሥነ ምህዳር ማስጠበቂያ ብልሃት በዘጌ ማኅበረሰብ

ሞገስ ሚካኤል[1]

## አኅጽሮተ ጥናት

ይህ ጥናት ትኩረቱ በጣና ሀይቅ ውስጥ በሚገኘው የዘጌ ባሕረ ሰላጤ ላይ ሆኖ በዋናነትም በባሕረ ሰላጤው በሚኖረው ማኅበረሰብ የሚሰሩ ስእሎችና ቅርጻቅርጾች ሥነ ምህዳርን ለመጠበቅ ባላቸው ሚና ላይ ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በዓላማ ተኮር ናሙና መረጃ ሰጪዎች ተመርጠው በአካባቢው ስለሚሰሩ ስእሎችና ቅርጻቅርጾች ተግባር መረጃዎች በምልከታ፣ በቃለመጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት ተሰብስበው በገላጭ ስልት፣ በ"Ecocriticism"፤ በሥነ ትእምርት (Semiotics) እና በተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ (Functionalism) ተተንትነዋል፡፡ በውጤቱም በዘጌ ስእል መሳልና ቅርጻቅርጽ መስራት የሥነ ምህዳር መጠበቂያ ብልሃቶች እንደሆኑ ታውቋል፡፡ እንዲህ የተደረገው በዋናነት በአካባቢው ገዳማትን መስርተዋል፤ አሁን ላለው ዘገኛ ማንነት መሰረት ጥለዋል ተብሎ ከሚታመንባቸው ከአቡነ በትረማርያም ጋር ተያይዘው ለሚነገሩ ተረኮችና በእሳቸው ዘመንም ሆነ እሳቸው ካለፉ በኋላ በአካባቢው ተፈጽመዋል፤ ለወደፊትም ይፈጸማሉ ተብሎ ለሚታመንባቸው ሃይማኖትን፣ ባህልንና ሥነ ምህዳርን ላስተሳሰሩ ትረካዎች ስእሎችንና ቅርጻቅርጾችን በትእምርትነት በማቆም ነው፡፡ እነዚህ ትእምርቶች የተለያዩ ገጽታዎች አሏቸው፡፡ አንዱ ገጽታቸው ስእል መሳልና ቅርጻቅርጽ መስራት በምድር በረከት፣ በሰማይ ጽድቅ የሚያስገኙ ሙያዎች ተደርገው እንዲቀጠሩ የቆመ ነው፡፡ ሌላው ገጻቸው ደግሞ ዘጌን በገነት በመመሰል፣ ሕይወት ያላቸውን ፍጥረታት (በዋናነት እጽዋትን) የጽድቅና የኩነኔ ተምሳሌት በማድረግና በአፈጣጠር ባሕርይ ከሰው ጋር በማዛመድ የተለየ አካባቢያዊ የአምልኮ ሥርዓት በመገንባት የቀረበ ሲሆን፣ ይህንን ሥርዓት ለማስጠበቅ እንደ መቅሰፍተ እግዚአብሔር የሚቆጠሩ መብረቅን፣ ነብርን፣ እባብን፣ ዘንዶንና ሌሎችንም መከራዎች በቅጣትነት በማቆም ተገልጿል፡፡ በረከቶችን በመሻት፣ ቅጣቶችን በመፍራት መካከል (Equilibrium) ሚዛን መጠበቁን፤ በተለይ እንስሳት የማይገደሉበት፣ ደን የማይመነጠርበት፣ የሰብል እርሻ የማይተገበርበት የዘጌ ተፈጥሯዊ አካባቢ (ሥነ ምህዳር) መመስረቱን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ እነዚህ በረከቶችና ቅጣቶች የቀረቡባቸው የአመሳሰል (representation) ሥርዓቶችም በግልጽ ታይተዋል፡፡

***ቁልፍ ቃላት***

*ስእል፣ ቅርጻቅርጽ፣ ሥነ ምህዳር፣ ተግባር፣ ዘጌ*

## መግቢያ

[1] PhD,Bahir Dar University ,Ethiopia; Email: mikydove74@gmail.com

የዘጌ ባሕረ ሰላጤ በጣና ሃይቅ ላይ ከሚገኙ አራት ባሕረ ሰላጤዎች (peninsulas[2]) መካከል አንዱና ትልቁ ነው፡፡ ይህ ባሕረ ሰላጤ ከጣና ሃይቅ በስተ ሰሜን ምእራብ አቅጣጫ ይገኛል (Getinet 2005: 22፤ አስቴር 2000፡ 52)፡፡

በዚሁ ሥፍራ ስምንት ጥንታዊ (ከነዚህ ውስጥ አንዱ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ እንደገና በመገንባት ላይ የሚገኝ)፣ አንድ ደግሞ በ2008 ዓ.ም የተቋቋመ በጥቅሉ ዘጠኝ ገዳማትና አድባራት[3] ይገኛሉ፡፡ የአካባቢው መሬትም በሀገር በቀል ጥቅጥቅ ደን የተሸፈነ ሲሆን በባሕረ ሰላጤው ውስጥ በሚኖረው ማኅበረሰብም ሆነ በገዳማውያኑ የቤት እንስሳት ማርባት፣ የዱር እንስሳትን መግደል፣ ደን መመንጠርና የሰብል እርሻ ማረስ በማኅበረሰቡ ባህል መሰረት የተከለከሉ ናቸው፡፡ በአንጻሩ ባህላዊ ስእሎች[4] መሳል፣ ባህላዊ ቅርጻቅርጾች መስራት፣ አትክልትና ፍራፍሬ ማምረት፣ ዓሣ ማጥመድ፣ ይፈቀዳሉ፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ተዳምረው የዘጌነት መገለጫዎች ሆነው ይታያሉ፡፡

ይህ ጥናት በስእልና በቅርጻቅርጽ አማካይነት ሥነ ምህዳር[5] እንዴት እንደሚጠበቅ የተነተነ ነው፡፡ በዋናነትም በዚህ ጥናት የዘጌ ማኅበረሰብ ሥነ ምህዳራዊ ጉዳዮች በስእልና በቅርጻቅርጽ አማካይነት የተገለጹባቸውና የተወከሉባቸው ትእምርቶች፣ ትእምርቶችም ማኅበረሰቡንና ሥነ ምህዳርን ያስተሳሰሩበት መንገድ፣ ይህ ትስስራቸው ደግሞ በሥነ ምህዳር ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ በጥልቀት መርምሯል፡፡

---

[2] ይህንን የእንግሊዝኛ ቃል ባሕረ ገብ፣ ባሕረ ሰላጤ፣ የባሕር ወሽመጥ በሚሉ አማርኛ ስያሜዎች ሲጠሩት መስማት የተለመደ ነው፡፡ የአማርኛ ስያሜ ቃላቱ የተለያዩ ይሁኑ እንጅ በትርጉም ሁሉም ባንድ በኩል ከዉኃማ አካል፣ በሌላ በኩል ከደረቅ መሬት የሚዋሰንን ሰፊ የመሬት ክፍል ገላጮች ናቸው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጽሑፍ ዘጌ እያልኩ የጠቀስኩት ሀሳብ ሁሉ ይህንን የመሬት ክፍል የሚገልጽ ነው፡፡

[3] ነዋሪዎቹ ገዳማት እያሉ ቢጠሯቸውም በአሁኑ ጊዜ አብዛኞቹ ወደቤተክርስቲያንነት በመቀየር ላይ ናቸው፡፡

[4] በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ባህላዊ ስእሎች እና ባህላዊ ቅርጻቅርጾች እያልኩ የምገልጻቸው ሀሳቦች በእንግሊዝኛ (እንደየቅደምተከተላቸው) “Folk arts” እና “Folk sculptures” በመባል የሚጠሩትን የቁሳዊ ባህል ዘርፎችን ነው፡፡ ምንም እንኳ አንደኛው ከሌላው የተሳሰሩ ቢሆንም “Folk arts” የሚለው ምድብ ባህላዊ ጥበባትን ለምሳሌ ስእሎችንና ባህላዊ ማስዋቢያዎችን (folk decorations) የሚያካትት ነው፡፡ “Folk sculptures” ደግሞ ከሸክላ፣ ከእንጨት፣ ከብረት፣ ከቆዳ፣ ከሳርና ከሌሎችም ነገሮች የሚቀረጹ የእጅ ስራዎች ሁሉ የሚካተቱበት ሰፊ ዘርፍ ነው (Green 1997: 56-60)፡፡

[5] ይህንን ቃል አንዳንዶች ዓለም፣ ተፈጥሮ፣ አካባቢ በማለት ገልጸውታል፡፡ ለምሳሌ Milton (1996: 24-27) “ecology, world, environment, nature” አንዱ ሌላውን መግለጽ የሚችል (ተተካኪ) አድርገው ጠቅሰዋል፡፡

ከአሁን ቀደም የተለያዩ አጥኚዎች ከተለያዩ ገዳማት አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች፣ ቁሳዊ ባህል፣ በዓል አከባበር፣ የገዳም ሥርዓቶችና የሃይማኖት ተቋማት ለደን ጥበቃ ባበረከቱት አስተዋጽኦ ላይ ጥናት አድርገዋል፡፡ ፍሬህይወት (በ2000 ዓ.ም) "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገጽታ"፤ አስቴር (በ2000 ዓ.ም) "ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በዘጌ ባሕረ ሰላጤ"፤ አንተነህ (በ2001 ዓ.ም) "በዳባት ገብርኤል ቤተመዘክር ውስጥ የሚገኙ ቁሳዊ ባህሎች መዘርዝር ከአጫጭር መግለጫ ጋር"፤ Abebaw (በ2002) "A history of painting in east Gojjam in the eighteenth and nineteenth centuries: A study of the 'second Gondarine' style of painting"፤ ምህረት (በ2003 ዓ.ም) "ከጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት"፤ ሞገስ (በ2003 ዓ.ም) "ከዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችና አምልኳዊ ስርዓቶች"፤ ሞገስ (በ2007 ዓ.ም) "በዘጌ ባህረ ገብ መሬት ላይ በሚገኙ ገዳማት ውስጥ የተሳሉ ጥንታዊ የግድግዳ ላይ ስእሎችና የአሳሳል ልማድ"፤ ወንድወሰን (በ2007 ዓ.ም) "በፃድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ጥናት"፤ ዮሴፍ (በ2007 ዓ.ም) "የደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ተረኮች ጥናት ክዋኔ"፤ መሪማ (በ2009 ዓ.ም) "የእንጦጦ ሐመረ ኖኀ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አመሰራረትና በገዳሟ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ትንተና"፤ Elisabeth (2009) "Contemporary Ethiopian Painting in Traditional Style Beginning and Change"፤ እንዲሁም Cutts et al. (2010) "The image revealed: Study and Conservation of a mid- nineteenth century Ethiopian church painting."፤ የሃይማኖት ተቋማት ለደን ጥበቃ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ በተመለከተ ደግሞ Alemayehu (ዓ.ም ያልተገለጸ) "Opportunities, Constraints and Prospects of Ethiopian Orthodox Tewahido Churches in Conserving Forest Resources: The Case of Churches in South Gondar, Northern Ethiopia."፤ Teferi (በ2008) "Forest conservation tradition of the Ethiopian Orthodox Tewahdo Church: The case of West Gojjam zone, North West Ethiopia"፡፡

ሁሉም አጥኝዎች በስእሎችና በቅርጻቅርጾች አማካይነት ሥነምህዳር እንዴት እንደሚጠበቅ አልተመለከቱም፡፡ ይህ ክፍተት መኖሩ ለዚህ ጥናት መካሄድ በር ከፍቷል፡፡

## የጽንሰ ሀሳብና የንድፈ ሃሳብ ቅኝት

በዚህ ክፍል ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጽንሰ ሀሳቦች፣ በጥናቱ ተግባራዊ የተደረጉ ንድፈ ሀሳቦችና አተገባበራቸው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**የጽንሰሀሳብ ቅኝት**

**በዚህ ንኡስ ክፍል ከጥናቱ ጋር የተገናኙ ጽንሰ ሃሳቦች ተቃኝተዋል፡፡**

**ስእል**

ኪነጥበብ የጥበብ ዘርፎች ሁሉ ጥቅል መጠሪያ ሆኖ በስሩ ሙዚቃ፣ ሥነ ጽሑፍ፣ ቅርጻቅርጽና ስእል እንደሚካተቱ ምሁራን ያነሳሉ (ብርሃኑ፣ 1999፤ እሸቱ፣ 2004)፡፡ በመሆኑም ስእል አንዱ የኪነጥበብ ዘርፍ ነው፡፡

እሸቱ (2004፡ 195) የስእል ምንነትን ሲያስረዱ እንዲህ ብለዋል፤

> … ስእል የአማርኛ ቋንቋ ከጥንታዊ የግዕዝ ቋንቋ እንዳለ በቁሙ የወረሰው ነገረ - ቃል (Terminology) ነው፡፡ … ስእል፡- በቁሙ፤ መልክ፣ የመልክ ጥላ፣ አምሳል፣ ንድፍ፣ ቢጋር፣ በውሃ፣ በመጽሔት፣ በጥልፍ፣ በስፌት ወይም በቀለም በወረቀት ገዝፎ፣ ተጽፎ ከጽብር፣ ከእብን፣ ከዕጽ፤ ከማዕድን፣ ታንጦ፣ ተቀርጦ፣ ተሸልሞ፣ ተጊጦ፣ የሚታይ የሚዳሰስ ነገር፡፡ … የስእል ጥበብ … የጥበብ አካል ነው፤ የባህልም፡፡ የስእል ጥበብ ባጭሩ ሲገለጽ፡- ደግሞ የአንድ ግለሰብ ወይም ኅብረተሰብ ወይም ሀገር የህሊናዊና የቁሳዊ ባህል ማንነት መገለጫና መለያ ነው፡፡ በመሆኑም የስእል ጥበብ በስርዓተ እምነትና ሃይማኖት፣ በስርዓተ እውቀትና ፍልስፍና፣ በስርዓተ ማኅበረሰብና አኗኗር ውስጥ የሚከሰት፣ ለህሊናዊና ለሰው ልጅ ሁሉ አገልግሎትና ጠቀሜታ የሚውል፤ እሴትና ፋይዳው የከበረና የላቀ፤ ታላቅ የባህል ሃብትና ቅርስ ነው፡፡

ከላይ ያለው ምንጭ እንደሚያመለክተው ስእል ሀሳብን በሚዳሰስ ነገር መግለጽ ነው፤ የአንድ ነገር መልክ ወይም ንድፍ ነው፡፡ የማንነት መገለጫና መለያም ነው፡፡ የሚሳለውም ከተክል፣ ከማዕድናት፣ ከውሃ፣ ወዘተ. በሚዘጋጁ ቀለማት ሆኖ በጥልፍ፣ በስፌት፣ በወረቀት፣ ወዘተ. ላይ ነው፡፡ የቀለማቱን ዝግጅትና የሚያርፉበት ቁስ አስመልክተው እሸቱ ከገለጹት ባሻገር ቀለማቱ ከአፈር፣ ከእንስሳት ልዩ ልዩ ተዋጽኦዎች ጭምር ሊዘጋጁ ይችላሉ፡፡ የሚያርፉበት ቁስ ደግሞ ጨርቅ፣ ብራና፣ ገበታ፣ ግድግዳ፣ ድንጋይ ላይም ሊሆን ይችላል (Abebaw 2002)፡፡

ባህላዊ ስእል ደግሞ አንድ ኅብረተሰብ በልማዳዊ እውቀት በመታገዝ፣ በቅርብ የሚያገኛቸውን ግብዓቶች በመጠቀም ለተለያዩ ተግባራት የሚስላቸውን ስእሎች የሚያካትት ሲሆን በዋናነትም ማኅበረሰቡ የሚከተለውን ሃይማኖት፣ ያለውን ታሪክ፣ ገጠመኝ፣ ፍልስፍና፣ ርዕዮተ ዓለም፣ ያሳለፈውን የሕይወት ውጣ ውረድ፣ ወዘተ. የራሱን ሀገር በቀል

ዕውቀትና አካባቢያዊ ቁሳቁሶችን በግብዓትነት በመጠቀም የሚስላቸው ስእሎች ናቸው፡፡

ባህላዊ ስእሎች ከሚገኙባቸው አካባቢዎች መካከል ዘጌና በዚያው የሚገኙ የሃይማኖት ተቋማት ይጠቀሳሉ፡፡ የዚህ ጥናት ማእከላዊ ትኩረትም በእነዚህ ስእሎች አማካይነት ሥነምህዳር እንዴት እንደሚጠበቅ መመርመር ነው፡፡

## ቅርጻቅርጽ

እንደ Green (1997: 56-60) አገላለጽ ባህላዊ ቅርጻቅርጾች ከእንጨት፣ ከድንጋይ፣ ከብረት፣ ከሳር፣ ከቀንድ፣ ከጭቃ፣ ከቆዳና ከመሳሰሉት ነገሮች በባህላዊ መንገድ የሚሰሩ የጥበብ ዘርፎች ናቸው፡፡ እነዚህ ቁሶች እንደ ቁሳዊ ባህል ዘርፍነታቸው የሰሪዎቻቸውንና የተጠቃሚዎቻቸውን ማንነት ገላጮች ናቸው፡፡ በተጠኚው ማኅበረሰብ ውስጥ ቅርጻቅርጾችን መስራት የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም አሰራራቸውና ተግባራቸው በዚህ ጥናት ተመርምሯል፡፡

## ሥነ ምህዳር (Ecology)

እንደ Anderson and Sutton (2010: 35) አገላለጽ ሥነ ምህዳር ወይም "Ecology" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የመጣው "oikos" እና "logos" ከሚሉ የግሪክ ቃላት ሲሆን ፍቺውም የመጀመሪያው መጠለያ "house" ወይም መኖሪያ "habitat" ማለት ሲሆን "logos" ደግሞ የጥናት መስክ "word/ academic discipline" ማለት ነው ፡፡

ይህ የጥናት መስክ የተፈጥሮና የፍጡራን ግንኙነት የሚመረመርበት ሰፊ የምርምር መስክ ነው፡፡ ሰውን፣ እጽዋትን፣ አየርን፣ ውሃን፣ አፈርን፣ እንስሳትን፣ ነፍሳትን፣ አእዋፍንና ሌሎችን የተፈጥሮ አካላትንና በእነዚህም አካላት መካከል የሚኖር ግንኙነትን ሁሉ ያጠናል፡፡

የሥነ ምህዳር ጥበቃ ሲባል ደግሞ የተፈጥሮ ሚዛንን መጠበቅ ነው፡፡ ህይወት ያላቸውንና ህይወት የሌላቸውን አካላት ከብክለት፣ ከብልሽት፣ ከጥፋት፣ ወዘተ. መጠበቅንና መንከባከብን ገላጭ ነው፡፡ የሥነ ምህዳር ሚዛን መዛባትም አንድ አካባቢ በአማካይ ሊኖረው ከሚገባ የሰው፣ የእንስሳት፣ የእጽዋት፣ የውሃ፣ የአየር፣ የአፈር፣ የርጥበት፣ የሙቀት፣ የዝናብ፣ ወዘተ. መጠን መቀነስ ወይም መጨመር ጋር ተያያዥ ነው (ወልደ አምላክ 2004፡ 22፤ ንጉሡ 2004፡ 5)፡፡ መቀነሱም ሆነ መጨመሩ የሥነ ምህዳር ሚዛኑ መዛባት መከሰቻዎች ሲሆኑ በሥነ ምህዳር ሚዛን አለመጠበቅ ምክንያት ህይወት ያላቸውም ሆኑ ህይወት የሌላቸው የተፈጥሮ አካላት ብርቱ ጉዳት ይደርስባቸዋል፡፡ ይህ እንዳይሆንና የሥነ ምህዳር ሚዛን ተጠብቆ እንዲሄድ በማድረግ ረገድ

ሃይማኖቶችና ባህላዊ የሥነ ምህዳር እውቀቶች ትልቅ ሚና እንደሚጫወቱ (Anderson and Sutton 2010: 105) ገልጸዋል፡፡ ባህላዊ ስእሎችና ቅርጻቅርጾች ደግሞ የሥነ ምህዳር እውቀት ምንጮች፣ የእውቀቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፊያዎችና መጠበቂያዎች ከመሆናቸው ባሻገር አመራረታቸውም ሆነ አጠቃቀማቸው ከሥነ ምህዳር ጋር ግንኙነት አለው፡፡ በመሆኑም በዘጌ ማኅበረሰብ በሚሰሩ ባህላዊ ስእሎችና ቅርጻቅርጾች አማካይነት የተገለጹ ሥነ ምህዳራዊ ጉዳዮች በዚህ ጥናት በዝርዝር ተነስተዋል፡፡

## የንድፈሀሳብ ቅኝትና አተገባበር

በጥናቱ ተግባራዊ የተደረጉት ንድፈሀሳቦች ሥነ ትእምርትና ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ናቸው፡፡

### ሥነ ምህዳራዊ ሂስ (Ecocriticism)

ሥነ ምህዳራዊ ሂስ (Ecocriticism) ከሁለት ቃላት ጥምረት የተገኘ ሲሆን እነዚህም ሥነ ምህዳር ወይም “eco” እና ሂስ ወይም “criticism” ናቸው (Glotflety and Fromm 1996: xx)፡፡ ይህ ስልት በሰው፣ በተፈጥሮ (በሥነ ምህዳር) እና በባህል መካከል ያለው መስተጋብር የሚመረመርበት ስልት ነው፡፡

ከባህል ጥናት አኳያ ሥነ ምህዳራዊ ስልት (Ecocriticism) አንድ ማኅበረሰብ ስለ ሥነ ምህዳር ያለውን እውቀት (Ecological knowledge)፣ አመለካከት (Attitude)፣ እንዲሁም ልማዳዊ ተግባራት (Cultural practices) ከመመርመሩም አልፎ በእነዚህ አካላት ማለትም በሰውና በተፈጥሮ አካላት (ሕይወት ባላቸውና ሕይወት በሌላቸው ፍጡራን) መካከል የሚኖር መስተጋብርንና እነዚህም መስተጋብሮች የተወከሉባቸውን መንገዶች መመርመር ላይ የሚያተኩር ስልት ነው፡፡ ይህ ስለ ሥነ ምህዳር ያለ እውቀት፣ አመለካከትና ልማድ ከመንፈሳዊና ከቁሳዊ ባህል ጋር የተሳሰረ ሊሆን እንደሚችል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ባህል በሥነ ምህዳር ላይ ወይም ሥነ ምህዳር በባህል ላይ ተጽእኖዎች እንደሚኖራቸውና የሥነ ምህዳራዊ ስልት (Ecocriticism) በእነዚህ እሳቤዎች ላይ እንደሚመሰረት Glotfelty and Fromm (1996: xx) ይገልጻሉ፡፡ በዚህ ጥናት ይህ ስልት የዘጌን ማኅበረሰብ ከተፈጥሮ፣ ተፈጥሮን ከማኅበረሰቡ ጋር በማስተሳሰር የተሳሉ ስእሎችና ቅርጻቅርጾችን፣ እነዚህ ቁሶች እንዲሰሩ መነሻ የሆኑ ተረኮችን ወይንም ቁሶችን መነሻ አድርገው የሚነገሩ ተረኮችንና የወከሏቸውን ትእምርቶች ለመለየትና ለመፈከር አገልግሏል፡፡

### ሥነ ትእምርት (Semiotics)

ይህ የጥናት መስክ ትእምርቶች ፍቺዎችን እንዴት እንደሚያመነጩ የሚያጠና ሳይንስ ሲሆን የሥነ ልሳናዊ ቋንቋ ትእምርቶችን፣ ቁስን፣ ሁነትን፣ ድርጊትን፣ ባህርይን፣ መልክን፣ ሥነ ልሳናዊ ያልሆኑ መግባቢያዎችን፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን፣ ወዘተ. እንደ ትእምርት ወይም ምልክት በማጤን የሚያጠና ሳይንስ እንዲሁም፣ እነዚህ ትእምርቶች ወይም ምልክቶችም በቀጥታ ከሚገልጹት ፍቺዎች የተለዩ ሌሎች ፍቺዎችን እንደሚያመነጩ "ትእምርቶች" ይመረምራል፡፡ ባህላዊ ቁሶችንም ከቁስነታቸው ያለፉ አካባቢያዊና ባህላዊ ስምምነት ያላቸውን ፍቺዎችን በመተርጎም ያጠናል (Berger 2010፤ Woodward 2007)፡፡ ይህም በመሆኑ እነዚህን ጉዳዮች ለማሳየት ጥናቱ የቁሶችን ወካይነት ለማሳየት እንዲሁም ለቁሳዊ ባህሎች መፈጠር በምክንያትነት የሚጠቀሱ ወይም ቁሳዊ ባህሎችን መነሻ አድርገው የሚነገሩ ተረኮችን ይዘትና ትእምርቶቻቸውን ለመመርመር ይህ ንድፈ ሀሳብ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

ሌላው በዚህ ጥናት ውስጥ የተተገበረው ንድፈ ሀሳብ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡

**ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ (Functionalism)**

እንደ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ አራማጆች አተያይ ማንኛውም የፎክሎር ዘርፍ በሚመረመርበት ወቅት የራሱ የሆነ ማኅበራዊ ተግባር አለው (Pearce 1994)፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ በቁሶች አማካይነት የተፈጠሩ አጠቃላይ መዋቅሮችን፣ የስእሎችንና የቅርጻቅርጾችን እንዲሁም የተረኮችን ተግባራት ለማስረዳትና ለማጉላት ንድፈ ሀሳቡ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

# የመረጃ ትንተና

በዚህ ክፍል በዘጌ የሚገኙ ገዳማትና አድባራት፣ በአካባቢው የሚሰሩ ስእሎችና ቅርጻቅርጾች ለሥነ ምህዳር ጥበቃና አጠቃቀም ዘርፍ ያበረከቷቸው ፋይዳዎች ተተንትነዋል፡፡ የተተነተኑ መረጃዎች ከመስክ በቃለመጠይቅ፣ በምልከታና በተተኳሪ የቡድን ውይይት የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ አተገባበራቸውን በተመለከተ ከዚህ ቀደም በምእራፍ ሶስት በዝርዝር የቀረበ ቢሆንም ለማስታወስ ያህል በቃለመጠይቅና በተተኳሪ የቡድን ውይይት የተሳተፉ ግለሰቦችና ተቋማት ሲመረጡ በዋናነት የገዳማቱን ታሪክ፣ በገዳማቱ ውስጥ እና በዙሪያቸው በሚኖረው ማኅበረሰብ የሚሰሩ ስእሎችንና ቅርጻቅርጾችን ምንነት፣ ታሪክ፣ ቁሶቹ ለማንነት ግንባታ፣ ተከላና ስርጸት እንዲሁም ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ወይም ብክለት የሚጫወቷቸውን አስተዋጽኦዎች በተመለከተ ቅርበትና እውቀት አላቸው ተብሎ የታሰቡ ናቸው፡፡ እነዚህም በገዳማቱ ውስጥ የሚኖሩ ገዳማውያን፣ የማኅበረሰቡ አባል የሆኑ አባቶችና እናቶች፣

የሥነ ጥበባት መምህራንና ተመራማሪዎች፣ የሥነ ምህዳር መምህራንና ተመራማሪዎች፣ የቁሶቹ ሰሪዎች፣ ሻጮችና ገዢዎች፣ የክልሉና የባሕር ዳር ከተማ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊዎች፣ የደንና አካባቢ ጥበቃ ባለሙያዎች እንዲሁም ሌሎች ርእሰ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ግለሰቦች ናቸው፡፡

ከተጠቀሱት ምንጮች የተገኙ መረጃዎች የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ በየፈርጃቸው ከተመደቡ በኋላ ከሌሎች ሰነዶች ከተገኙ መረጃዎች ጋር እየተናበቡ ተተንትነዋል፡፡

የዘጌ ገዳማትና አድባራት በውስጣቸውና በአካባቢያቸው በርካታ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ቅርሶች ይገኙባቸዋል፡፡ እነዚህን ቅርሶች መነሻ በማድረግ ሃይማኖታዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ይዘት ያላቸው ስእሎችና ቅርጻቅርጾችን በማምረት እንዲሁም ለገበያ በማቅረብ የሚተዳደሩ የማኅበረሰቡ ክፍሎች ብዙ ናቸው፡፡ ገዳማቱና በአካባቢው የሚመረቱ ቁሶች ለሥነ ምህዳር ጥበቃና አጠቃቀም ዘርፍ ጉልህ ሚና የሚጫወቱ ናቸው፡፡ ይህንን ሚና እንዲጫወቱ የረዱ ዋና ባህላዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ስእልንና ቅርጻቅርጽን ጨምሮ በተለያየ መንገድ እየቀረቡ ገዳማውያኑና የአካባቢው ማኅበረሰብ ከሥነ ምህዳር ጋር ሚዛናዊ ግንኙነት እንዲኖራቸው አድርገዋል፡፡ ይህ ግንኙነታቸው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## የዘጌ ሥነ ምህዳር ጥበቃና አጠቃቀም ልማድ መሰረቶች

የዘጌ ማኅበረሰብ ስለሰውና ስለተፈጥሯዊ አካባቢ (ሥነ ምህዳር) ያለውን ባህላዊና ሃይማኖታዊ እሳቤ በተለያዩ መንገዶች ገልጾ ይገኛል፡፡ ስእሎችና ቅርጻቅርጾች ዋነኞች ናቸው፡፡ እነዚህ ስእሎችና ቅርጻቅርጾች በአካባቢው ተፈጽመዋል፤ ወደፊትም ሊፈጸሙ ይችላሉ ተብሎ የሚታመንባቸውን ተረኮች መነሻ አድርገው የቀረቡ ናቸው፡፡ በመስክ ስራ ይህ ባህርይ የሚታይባቸው የተለያዩ ተረኮች የተሰበሰቡ ሲሆን ይዘታቸውን ስናይ በሰውና በተፈጥሯዊ አካባቢ (ሥነ ምህዳር) መካከል ያለ መስተጋብርን የሚያሳዩ፣ የሥፍራውን ስያሜና የገዳማቱን አመሰራረት የሚገልጹ፣ የሥፍራውን ቅድስና የሚገልጹ፣ የሃይማኖቱን መስፋፋት የሚያሳዩ፣ በሥፍራው የተፈጸሙ ተዓምራትን የሚናገሩ፣ በፈጣሪ እና በገዳማቱ መስራች አባቶች ለሥፍራው የተገቡ ቃልኪዳኖችን የሚገልጹ ወይም ለአካባቢው ማኅበረሰብ የተፈቀዱና የተከለከሉ ሥርዓቶችን የሚያሳዩ፣ በሥፍራው የሚገኙ የከበሩ ቁሶችን የሚገልጹና የነገሥታትን ጉብኝት ተራኪዎች ሆነው እናያለን፡፡ የተረኮቹ ተቀዳሚ ዓላማ የእምነት መሰረቶችን ለመግለጽ፣ የተከታዮችን ቁጥር ለማብዛትና እምነቶችን ለማስፋፋት፣ የእምነት መሰረቶችን ለማስረጽ እና የተገነቡት ሥርዓቶች ተጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፉ ለማድረግ

ሲባል ሲተረኩ የኖሩ ቢሆንም በሂደት ከባህል ጋር በተለያዩ መንገዶች በመዋሃድ ሥነ ምህዳሩን ያስጠበቁ፣ ከሥነ ምህዳር ጥበቃ ጋር የተያያዘ የተለየ ማኅበራዊ ማንነት (ዘገኛነትን) የገነቡ ናቸው፡፡

እነዚህ ተረኮች የዘጌ ስያሜ መነሻ ምክንያት፣ ህግና ሥርዓት መገኛዎች፣ የማኅበረሰቡ መተዳደሪያ ምንጭ፣ ወዘተ. ሆነዋል ተብሎ ከሃይማኖት፣ ከባህል፣ ከሥነ ምህዳር (ተፈጥሯዊ አካባቢ) ጋር የተቆራኙ ሲሆኑ የዘጌ ገዳማትን እንዳቋቋሙ ከሚነገርላቸው አባ ናሆምና አቡነ በትረማርያም ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ናቸው፡፡ የሚከተሉትን በምሳሌነት እንመልከት፤

ተረክ 1

> አቡነ በትረማርያም በሸዋ ክፍለ ሀገር ከምትገኘው ሰብላ ከምትባል ሀገራቸው ሲወጡ ከአንዲት ጌሾ በትር ሌላ የያዙት የለም፡፡ ስትጓዙ ከበትራችሁ በስተቀር ሌላ ለእግራችሁ ጫማ፣ ለጉዟችሁ ስንቅ አትያዙ የተባለውን የወንጌል ቃል ሐዋርያዊ ጉዞ በማሰብ እርሳቸውም በጎጃም፣ በዳሞት፣ በአገው ምድር፣ በጎንደርና በደንቢያ ብዙ ገቢረ ተዓምራት ሲያደርጉባት ቆይተው በኋላ የመጨረሻ ቃል ኪዳን ቦታ አለች ተብለው በመልአኩ ቃል ተነግረው የጣናን ባህር እንደመርከብ አድርገው ተሻግረውባት መጡ፡፡ በዚያ የነበሩ መነኮሳት ተደንቀው "አባ በምን መጡ?" ሲሏቸው "በዘንጌ" አሉ፡፡ "በዘንጌ" ሲባል ኖሮ በሂደት ዘጌ ሆነ (መጋቤ ሐዲስ ሰማኸኝና አባ ገብረሥላሴ፣ቃለመጠይቅ፣ 10/7/2011)፡፡

ተረክ 2

> አቡነ በትረማርያም እና ስድስቱ አባቶች ወንድሞቻቸው ባንድነት ሰባቱ ከዋክብት ተብለው ይጠራሉ፡፡ እነሱም ከሸዋ ክፍለ ሀገር ወጥተው የጣና ገዳማትን ያቀኑ ናቸው፡፡ አቡነ በትረማርያም ዘጌን፣ አቡነ ሂሩተ አምላክ ዳጋ እስጢፋኖስን፣ አቡነ ያሳይ መንዳባ መድኃኔዓለምን፣ አቡነ ዘካርያስ ደሴተ ገሊላን፣ አቡነ ያፍቅረነ እግዚእ ጉጉቤ ገብርኤልንና ጣና ቂርቆስን፣ አቡነ ታዴዎስ ደብረማርያምን፣ አቡነ ዘዮሐንስ ክብራን ገብርኤልን አቅንተዋል፤ ገድመዋል (አባ ገብረሥላሴ፣ ቃለመጠይቅ፣ 2/7/2011)፡፡

ተረክ 3

> ገዳመ ዘጌ የጸናችው በአባ ናሆም ነው፡፡ የአባ ናሆም ታሪክ ከአብርሐ ወአጽብሐ በኋላ፣ አንደኛ ረድፍ፣ ሁለተኛ አሞሲን እና

> ሶስተኛ ሳልሳይ የተባሉ ነገሥታት ከነገሱ በኋላ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ አባታችን አባ ናሆም በኢየሩሳሌም ዝጋግ በተባለች ደሴት በጸሎት እንዳሉ፣ የልዑል እግዚአብሔር መልአክ ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄዱ አዘዛቸው፡፡ በመጡም ጊዜ የነበሩበት ቦታ በእግዚአብሔር ኃይል ከእሳቸው ጋር መጥቶ በጣና ሃይቅ እንደተቀመጠ ይነገራል፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ዝጋግን ለማስታወስ ሲባል ይህ ቦታ ዘጌ ተባለ (አባ ገብረሥላሴ፣ ቃለመጠይቅ፣ 7/7/2011)፡፡

ከዚህ በላይ በቀረቡት ተረኮች እንደተገለጸው ተረኮች ገዳማቱን ቆርቁረዋል፤ የአካባቢው ስያሜ መነሻ ምክንያት ሆነዋል ተብለው የቀረቡ ናቸው፡፡ ተረኮቹ ልዩነት ይታይባቸው እንጅ ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ዘርፉ ያበረከቱት ጠቀሜታ አለ፡፡ ይህም ባንድ በኩል ባሕረ ሰላጤው በአባ ናሆም ልመና እና ጸሎት ምክንያት ከኢየሩሳሌም ተቆርሶ እንዳለ መጥቶ እንደተቀመጠ፣ በሌላ በኩል አካባቢው ለአባ ናሆምም ሆነ ለአቡነ በትረማርያም ቃልኪዳን የተገባለት ቅዱስ ሥፍራ ነው ተብሎ በገዳማውያኑና በአካባቢው ማኅበረሰብ እንዲታመን ማድረጋቸው ነው፡፡ በተጓዳኝም ገዳማውያኑም ሆኑ የአካባቢው ማኅበረሰብ ቅዱሳኑንና ቅዱሱን ሥፍራ ዘጌን እንዲወዱ፣ እንዲያከብሩና እንዲፈሩ አድርገዋል፡፡ ሥፍራውን መውደድ፣ ማክበርም ሆነ መፍራት ሁሉም ተዳምረው የአካባቢው ሥነ ምህዳር በከፍተኛ ደረጃ እንዲጠበቅ አድርገዋል፡፡ እነዚህ ለአካባቢ ሥነ ምህዳር መጠበቅ መሰረቶች የሆኑ አካባቢውን የመውደድ፣ የማክበርና የመፍራት ስሜቶች ደግሞ ምንጫቸው ተረኮች ናቸው፡፡ ይህንን አገላለጽ የሚያጠናክርልን በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ ገዳማትን መቆርቆር የጀመሩ፣ ብዙ ተአምራት የፈጸሙ፣ የገዳማቱንና የአካባቢውን ማኅበረሰብ በቃልኪዳን ያስተሳሰሩ፣ ህግና ሥርዓትን ያወጡ ናቸው ተብሎ በስፋት ስለሚታመንባቸው ስለ አቡነ በትረማርያም የተነገሩ[6] ተረኮችን ስንመለከት ነው፡፡ የሚከተሉት ናቸው፡፡

ተረክ 4

> አቡነ በትረማርያም ከገዳመ ዘጌ በጾም በጸሎት ተወስነው ሲኖሩ የመነኮሳት ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበዛ በመሄዱ በዚች ቦታ እርሻ፣ ቁፋሮ መሆን የለበትም፤ በደን የተሸፈነች ገነት መሰል ገዳም መሆን አለባት ሲሉ፣ እነዚህ መነኮሳት ምን ተመግበው ሊኖሩ ይችላሉ ብለው ወደ አምላካቸው በጸሎት አመለከቱ፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በአካል ተገልጦ እሷን የያዝካትን በትር ባርከህ ከሶስት ከፍለህ (ሰብረህ) ለረዳትህ

[6] ለቦታው ስያሜ መነሻ ሆነዋል ተብለው የሚነገሩትን ሁሉ ይጨምራል፡፡

ለበርተሎሚዎስ ስጠውና ከሶስት ቦታ ሲተክላቸው ጸድቀውና ለምልመው ለዘጌ ህዝብ መተዳደሪያ ይሆናሉ ብሎ ቃል በቃል አነጋገራቸው፡፡ እርሳቸውም እንደታዘዙት በትራቸውን ባርከውና ከሶስት ከፍለው ለረዳታቸው ለበርተሎሚዎስ ሲሰጡት ሲተክላቸው ለምልመው አንዷ ቡና፣ አንዷ ጌሾ፣ አንዷ ሎሚ ሆነው ጸድቀዋል፡፡ እነዚህም ሶስቱ እጽዋት እስከ ዓለም ፍጻሜ ለገዳመ ዘጌ ህዝብ መጠቀሚያ እንዲሆኑና በገዳሙ ውስጥ ሌላ ስራ እንዳይኖር፣ ጅራፍ እንዳይጮህ፣ እንስሳት እንዳይረቡ ብለው ሥርዓት ወስነዋል፡፡ አሁንም የዘጌ ህዝብ ዛሬም ቢሆን በቡና፣ በጌሾ እና በሎሚ፣ በደን ውጤቶች ብቻ በመጠቀም ሲተዳደሩና ምንም ዓይነት እርሻ እንደሌለ ከቦታው ድረስ የመጣው ሁሉ ሊያስተውለው የሚችል ሀቅ ነው (መሪጌታ አቤ እና መጋቢ ሐዲስ ሰማኸኝ፣ ቃለመጠይቅ፣ 29/7/2011)፡፡


ተረክ 5

አቡነ በትረማርያም በጾም በጸሎት ለ23 ዓመታት በገዳመ ዘጌ ሲጋደሉ የጸሎት ልብሳቸው ከብረት የተሰራ ነበር፡፡ በዚህም ሁኔታ ከኖሩ በኋላ እለተ እረፍታቸው ሲደርስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእልፍ አእላፍ መላእክት ጋር ወርዶ ወዳጄ በትረ ማርያም ሆይ በዛሬ እለት አንተን ከሃዘን ወደ ደስታ፣ ከህመም ወደ ህይወት ልወስድህ ነፍስህን አሳርፍ ዘንድ መጣሁ፤ ቦታህን የጻድቃን ማደሪያ እንደሆነችም እንደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት አደረኩልህ፡፡ በስምህ ቤተክርስቲያን የሰራ፣ እጣን የቋጠረ፣ መባ ያቀረበውን፣ ያንተ ስጋ የተቀበረበትን፣ አጽምህ ያረፈበትን፣ ገዳመ ዘጌ የተሳለመውን፣ ወንድ በአርባ ቀን፣ ሴት በሰማንያ ቀን በቦታህ ጥምቀተ ክርስትና የተቀበለውን፣ ከቤተክርስቲያንህ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስጋ ወደሙ የተቀበለ፣ በስምህ ገድልህን የጻፈ ጆሮ ያልሰማውን፣ ዓይን ያላየውን፣ ልብ ያላሰበውን፣ እንደአንተ ላለው አባቴ ያዘጋጀውን አወርሰዋለሁ፡፡ በገዳመ ዘጌ ላይ መብረቅና ነጎድጓድ፣ በምድር የሚሳቡ በመርዛቸው ሰውን የሚነድፉ እባቦች፣ በእግራቸው የሚሽከረከሩ አራዊት ሁሉ በአንተ ያመነውን አይጣሉም፡፡ በገዳማቱ የሚኖሩ መነኮሳትና ምእመናን እንደ መላእክት ኃጢአት የሌለባቸው ይሁኑ፡፡ በገዳመ ዘጌ ከመቃብርህ ላይ አፈር ቆንጥሮ የተቀባ ከህመሙ ይፈወስ፡፡ መቃብርህን እጅ የነሳ፣ የኔን መቃብር እጅ የነሳ ይሁንልህ ብሎ አስራ ሁለት የክብር አክሊል አቀናጅቷቸው ጌታችን ከመላእክቱ ጋር ወደ ሰማይ አረገ፡፡ ለአባታችን በተነገረው መሰረት አቡነ በትረማርያም ረዳታቸውን አባ

> በርተሎሜዎስን አስጠርተው መነኮሳት አሰብስበው እንዲህ ሲሉ መልእክት አስተላለፉ፤ "የእኔ የእረፍት ጊዜ ደርሷልና በገዳሙ ስትኖሩ ጹሙ ጸልዩ፤ የእግዚአብሔር ሰንበቱን አክብሩ፤ በመጨረሻው ዘመን ወደገዳሙ ክፉ ሰዎች ይመጣሉና ከእነሱ ተጠበቁ፡፡" ይህንን ሲሏቸው መነኮሳቱ ማን አባት ይሆነናል? ማንስ ከሃዘናችን ያረጋጋናል? ማንስ በጸሎት ይረዳናል? እያሉ አዘኑ፤ አለቀሱ፡፡ እሳቸውም እንደ "እኔ በርተሎሜዎስ አባት ይሁናችሁ" አሏቸው፡፡ ከዚህ በኋላ … በእለተ አርብ ከቀኑ 3 ሰዓት በ89 ዓመት ከ6 ወር ከ27 ቀን በዚያው መህል ዘጌ አረፉና አባ በርተሎሜዎስ 500 ቅዱሳን መነኮሳት አሰባስበው በድነ ስጋቸውን በቅዱሳን ህግ ገንዘው በሥርዓት በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ምስራቃዊ አቅጣጫ አስቀምጠው በዚያው ላይ የአቡነ በትረማርያም ቤተክርስቲያንን መሰረቱ፡፡ … በዚህ ስጋቸው ባረፈበት በቤተክርስቲያናቸው በአሁኑ ሰዓት በተሰጣቸው ቃል ኪዳን መሰረት ከመቃብራቸው አፈር ቆንጥሮ እምነት የተቀባ ስኳር በሽታ፣ ኪንታሮት፣ ቁንጭር፣ ካንሰር፣ ሌላም የተለያዩ በሽታዎች እየዳኑ ገቢረ ተአምሩን እየተናገሩ ሐምሌ 17 ቀን የንግሥ በዓላቸው እለት ስእለታቸውን ሲያስገቡ ይታያሉ (መሪ ጌታ አቤ እና መጋቢ ሐዲስ ሰማኸኝ፣ ቃለመጠይቅ፣ 29/7/2011)፡፡

ከላይ በቃል ከቀረቡት በተለይም ስለ አቡነ በትረማርያም ከሚነገሩ ተረኮች ጋር ተቀራራቢ የሆኑ ስእሎችም በስፍራው ተገኝተዋል፡፡ የሚከተለው ስእል አንዱ ማሳያ ነው፡፡

**ፎቶግራፍ ቁጥር 1፡- ተረኮች በስእል ሲገለጹ**




ምንጭ፡- በመስክ ስራው ወቅት በተመራማሪው የተነሳ

ከዚህ በላይ ገዳማቱን ስለመሰረቱ በተለይም ስለ አቡነ በትረማርያም በስፋት ከቀረቡት ተረኮች[7] ውስጥ እንደተገለጸው የዘጌ ማኅበረሰብ አጠቃላይ ማንነት እንዲሁም የሰውና የሥነ ምህዳር ጉዳዮች በእነዚህም መካከል ያለ መስተጋብር ከአንድ "anthropomorphic" ጉዳይ መንጭተው

[7] ተረኮቹ በቃል እንዲሁም በስእልና በቅርጻቅርጽ የቀረቡ መሆናቸውን ልብ ይሏል፡፡

በዚያውም ተወክለው እናገኛለን፡፡ ይህም “anthropomorphic” ጉዳይ በትር[8] ነው፡፡

በትር በብዙው ኢትዮጵያዊ ልማድ ውስጥ ባህላዊም ሃይማኖታዊም ተግባራትና ውክልናዎች አሉት፡፡ ባህላዊ ተግባሩንና ውክልናውን ስናይ በትር በእርጅና እና ድጋፍ ባስፈለገ ጊዜ ሁሉ ሶስተኛ እግር ነው፡፡ ለአቅመ ደካማ ምርኩዝ ወይም ድጋፍ ነው፡፡ ቅቤ ተቀብቶ፣ ጭስ ጠጥቶ፣ ተኾጎርጉሮና ተሸልሞ፣ ጫፉ ላይ ጀንፎ (ብረት) ተሰክቶበት ሲያዝ ደግሞ አንድም ጌጥንና ማኅበራዊ ክብርን ማሳያ (የኩሽ ሕዝቦች መለያ የሆነው የአባ ገዳ በትር፣ የባሌው የሼክ ሁሴን ዶንቄ፣ የአርሲ እናቶች ስንቄ፣ በየክብረ በዓላቱ በሀገር ሽማግሌዎችና የጎሳ መሪዎች የሚያዙት በትሮች፣ በየባህል ውዝዋዜውና ሙዚቃው በማድመቂያነትና በማስዋቢያነት በባህል ባለቤቶች ተይዘው የምናያቸው በትሮች ምሳሌዎች ይሆናሉ)፣ አንድም ነውጠኛነትንና በዚያውም የሚገኝ የሥነ ልቡና የበላይነትን ወካይ ይሆናል፡፡ ይህ ቁስ በመጠኑ፣ በመልኩ፣ በተሰራበት የእንጨት ዝርያ፣ በሚያዝበት ወቅት፣ በአያያዝ፣ በአገልግሎት አንዱ ከሌላው የተለየ፣ እያንዳንዱም የራሱ የሆኑ የተለያዩ ትእምርቶች ያሉት ነው፡፡ በዚህ ረገድ “Ulee” ወይም ዱላ ማኅበራዊ ደረጃን፣ ክብርን፣ ጾታን፣ እድሜን፣ ሁሉ በመወከል ግላዊና ማኅበራዊ ማንነት እንዴት እንደሚገነባ ለማወቅ “sticks, self and society in Borana Oromo” የሚለው የAneesa እና የGemetchu ጥናት ጥሩ ማሳያ ይሆናል (ዝርዝሩን Aneesa and Gemetchu in Arnoldi 1996: 145-166 ይመለከቷል)፡፡

በትር ከዚህ ልማዳዊ ውክልናውና ተግባሩ ባለፈ በተረኮቹ ውስጥ የዘጌ ማኅበረሰብ ከሃይማኖት፣ ከባህልና ከተፈጥሮ ጋር በእጅጉ እንዲናበቡ ከረዱ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ሆኖ እናገኛለን፡፡ ይህ በትር በተረኮቹ ውስጥ ተደጋግሞ እንደተነሳ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም ይኸው ቃል ዘጠና ዘጠኝ ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በትር የሚለው ቃል ይህን ያህል ጊዜ የተጠቀሰ ቢሆንም የተሰጡት ሃይማኖታዊ ውክልናዎች በዋናነት ከኃይል (power) ጋር የተዛመዱ ናቸው፡፡ ይህ ኃይል (power) በፈጣሪ የመመረጥ ምሳሌ፣ በፈጣሪ ለተመረጡት የዘለዓለም ርስት ወይም መንግሥት መግለጫ፣ ዋስ ጠበቃ ወይም መያዣ፣ የጽኑ እረኛ መለያ ወይም መጠበቂያ፣ ከፈጣሪ የተሰጠ ህግና ሥርዓት፣ በፈጣሪ እርዳታ የማሸነፍ ኃይል ወይም የጦር መሳሪያ፣ የቁጣና የመዓት ምልክት፣ ድጋፍ ወይም ምርኩዝ፣

[8] ኪዳነ ወልድ በትርን ሲበይኑት “ዘንግ፣ ሽመል፣ ምርኩዝ፣ ጎመድ፣ ከንተሮ፣ መንደርቶ፣ ለበቅ፣ ጨንገር” በማለት ነው (1948፡ 293)፡፡

ሥልጣን፣ ተዓምራት መከወኛና ቃልኪዳን ማጽኛ በሚሉ ዐበይት ጉዳዮች አማካይነት የተገለጠ ነው፡፡ እነዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለበትር የተሰጡ ውክልናዎች ስለአቡነ በትረማርያም በሚነገሩ ተረኮች ውስጥም ይንጸባረቃሉ፡፡ በትር ብዙ ነገር የመፈጸም ኃይልን (power) ወርሶ ይታያልና፡፡

ይህ በበትር የተመሰለ ታላቅ ኃይል እንደ ጀልባ ሆኖ ባሕር (ሃይቅ) አሻግሯል፡፡ አትክልትና ፍራፍሬዎች እንዲሁም የእደ ጥበብ ምርት የአካባቢው ማኅበረሰብ ዋነኛ መተዳደሪያዎች እንዲሆኑ ምንጭ ሆኗል፡፡ በትር በሁለት ጽንፍ የቆሙ በረከትና ቅጣት የሚሉ ሥርዓቶችንና ህጎችን መስርቷል፤ አጽንቷልም፡፡ በትር የተበጁትን ምድራዊና ሰማያዊ ሥርዓቶች የጠበቁትን መጠበቂያ፣ ያልጠበቁትን አንዴ ከበትርነት ወደ ሌሎች ምድራዊ ቅጣቶች ማለትም እንደ ነብር፣ ዘንዶ፣ እባብ እየተለወጠ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሰማያዊ ቅጣት (መብረቅ) እየሆነ መቅጫ ትእምርት ሆኖ ቆሟል፡፡ በትር እንዲህ “anthropomorphic” ጉዳይ ሆኖ ዘጌን መስርቷል፤ ዘገኛነትን አስገኝቷል፡፡ እነዚህን ሀሳቦች በዝርዝር እንመልከት፡፡

በተረኮቹ ውስጥ አቡነ በትረማርያም ለዘጌ ማኅበረሰብ እንደ ሙሴ ሆነው ቀርበዋል፡፡ ይኸውም አቡነ በትረማርያም እስራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት ነጻ ካወጣቸው ከሙሴ[9]፣ ጣና ሃይቅ ከቀይ ባሕር፣ የሁለቱም በትር አንደኛው ቀይ ባሕርን መክፈያ፣ ሌላው ጣናን መሻገሪያ ተደርገው ቀርበዋል፡፡ እንደ ሙሴ በትር ሁሉ የአቡነ በትረማርያም በትር የምድራዊና የሰማያዊ ህይወት ድጋፍ ወይም ምርኩዝ ሆኗል፡፡

የአቡነ በትረማርያም በትር በእጅ ተይዞ ከጎን የወይን ዘለላ በማውጣት ለአማኙ ምግብ፣ ለህሙማን መፈወሻ ሆኗል ተብሎ ይታመናል፡፡ እዚህ ላይ የአቡኑ በትር “ሙሴ ከአስራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች አንዳንድ በትር አምጥቶ በሁሉም ላይ የእያንዳንዱን ስም ጽፎ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ እንዲያኖራቸው በእግዚአብሔር ታዘዘ፡፡ ከነዚህ በትሮች አንዷ የአሮን ነበረች፡፡ አቆጥቁጣ፣ ለምልማ፣ አብባ፣ የለውዝ ፍሬ አፍርታ ተገኝታለች” (ዘኁ. 17፥ 1-11) ከሚለው ከአሮን በትር ጋር ተነጻጽሯል፡፡ ልዩነታቸው የአሮን ለውዝ፣ የአቡነ በትረማርያም ወይን ማፍራታቸው ነው፡፡ ልምላሜ ግን ያመሳስላቸዋል፡፡ የአቡነ በትረማርያም በትር በእጅ ተይዞ የወይን ዘለላ እያፈራ፣ ከሶስት ተከፍሎ በተተከለም ጊዜ የዘጌ ማኅበረሰብ የህልውና ማጠንጠኛዎች የሆኑ

[9]ሙሴ እስራኤላውያን በግብጾች በባርነት ተይዘው ለአራት መቶ ሰላሳ ዓመታት ከኖሩ በኋላ ቀይ ባሕርን በመክፈል ነጻ ያወጣቸው ቅዱስ ነው (ዘጸ. 12፥ 41-42)፡፡

እጽዋት (የቡና፣ የጌሾና የሎሚ) ሁሉ መገኛ ምንጭ ሆኗል ተብሎ ይታመናልና፡፡

ከፍ ብሎ በቀረቡት ተረኮች እንደተገለጸው በትር “ … ቦታህን የጻድቃን ማደሪያ እንደሆነች እንደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት አደረኩልህ፤ ከቃልህ ያልወጣውን ገነትን አወርሰዋለሁ፤ መብረቅ፣ አራዊቶችና እባቦች በአንተ ያመነውን አይጣሉም፤ በገዳሙ የሚኖሩ መነኮሳትና ምእመናን እንደ መላእክት ኃጢአት የሌለባቸው ይሁኑ፤ ከመቃብርህ አፈር ቆንጥሮ የተቀባ ከህመሙ ይፈወስ፤ መቃብርህን እጅ የነሳ የኔን መቃብር እጅ የነሳ ይሁንልህ” በማለት በፈጣሪና በአቡነ በትረማርያም መካከል ለተገባ ቃል ኪዳን የቆመ ትእምርት ነው፡፡

በተጨማሪም አቡነ በትረማርያም ለአካባቢው ማኅበረሰብ ዘለዓለማዊ መተዳደሪያዎች እንዲሆኑ “ዘጌ በደን የተሸፈነች ገነት ትምሰል፤ ቡና፣ ጌሾና ሎሚ የአካባቢው ህዝብ ዘለዓለማዊ መተዳደሪያዎች ይሁኑ” ሲሉ ያበጇቸው ሥርዓቶችና “በቦታውም እርሻ፣ እንስሳት ማርባት፣ አደን አይኑር፤ ከቃሌ የወጣውን መብረቅ፣ ነብር፣ እባብ አይለፉት” ግዝቶች ማጽኛም ነው፡፡

በመሆኑም የአቡነ በትረማርያም በትር የአካባቢው መጠሪያ መነሻ በመሆን፣ የተዓምራት መከወኛ በመሆን፣ የዘጌ ማኅበረሰብ የሶስቱ ዋነኛ መተዳደሪያዎች ማለትም የጌሾ፣ የቡና፣ የሎሚ ማስገኛ በመሆን፣ ምድራዊና ሰማያዊ ተስፋን በመስጠት የቃልኪዳን ማጽኛ ማለትም ዘጌ ዳግማዊት ኢየሩሳሌም፣ የሰማያዊት ኢየሩሳሌም ወይም የገነት ምሳሌ፣ የተሰወሩ ቅዱሳን መኖሪያ፣ ምድራዊና ሰማያዊ ቃልኪዳን የተገባላቸው ፍጡራን መኖሪያ፣ ሥፍራውን መጥቶ የጎበኘ፣ በሥፍራው እንዲከወኑ የተፈቀዱ ሃይማኖታዊ ተግባራትን የፈጸመ ሁሉ ስጋዊና መንፈሳዊ ፈውስ የሚያገኝበት ቅዱስ ሥፍራ ነው ተብሎ እንዲታመን አድርጓል፡፡ እንዲህም ስለሆነ በዚህ ሥፍራ የበቀለ በሰው እጅ አላግባብ አይነቀልም፤ የተወለደ አይገደልም፤ የቅዱሱ ሥፍራ፣ የገነት አምሳል፣ የዘጌ አካል ተደርጎ ይቆጠራልና፡፡ ይህም የሆነው በትርን ወደ ሌሎች ትእምርቶች ማለትም በረከቶችና ወደ መብረቅ፣ ነብር፣ እባብ፣ እንዲሁም ወደ ሌሎች መቅሰፍተ እግዚአብሔር ሁሉ በመለወጥ ነው፡፡ ይህ የአቀራረብ መንገድ ባንድ በኩል በትርን ወደ ብዙ ነገር በመለወጥ በትርን “anthropomorphic” አድርጎታል፡፡ በሌላ በኩል የተጠቀሰው በትር የማኅበረሰቡ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሥነ ምህዳራዊ ማንነት ምንጭ በመሆን በዘጌ ተፈጥሯዊ አካባቢ (ሥነ ምህዳር) የሚገኙ ህይወት ያላቸውና ህይወት አልባ ፍጥረታት የቅዱሱ የዘጌ አካል ተደርገው እንዲታዩ በማድረግ ይህ በትር በሥፍራው የብዙ

ጉዳዮች መሰረት ሆኗል፡፡ ራሱ በትርም ሆነ ከበትር ተገኝተዋል ተብለው የሚታመንባቸው ጉዳዮች ሁሉ እንደ ቅዱስ ነገር /totem/ ይቆጠራሉ፡፡

ከላይ ከቀረቡት “anthropomorphic” ጉዳዮች በተጨማሪ በቃልም ይሁን በስእልና በቅርጻቅርጽ በቀረቡ ተረኮች ውስጥ መንፈሳዊ አባቶችና እናቶች ከፍተኛው መንፈሳዊ የብቃት ደረጃ ሲደርሱ አራዊት ሲጠብቋቸው፣ ሲረዷቸው ወይም ቅዱሳኑ ወደ ሌላ ፍጡር ሲለወጡ የሚያሳዩ ስእሎችና ቅርጻቅርጾች በአካባቢው በብዛት ይገኛሉ፡፡ ለአብነት ያህል አቡነ አረጋዊ በዘንዶ ተጭኖ ተራራ ሲወጣ፣ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሰውነቱ በለስላሳ ነጭ ጸጉር ተሸፍኖ፣ አቡነ ሳሙኤል አንበሳ ሲጋልብ፣ ተክለሃይማኖት አክናፍ አውጥቶ፣ መጥምቁ ዮሐንስ በበረሃ ሳለ ቶራ (አጋዘን መሰል እንስሳ) እየጠባ፣ ሰውነቱ በግመል ጸጉር ተሸፍኖ፣ አንበጣ እየበላ እንዳደገ የሚገልጹ ስእሎች አሉ፡፡ በገዳማቱ የቤተ መቅደስ ግድግዳዎች ሰሜን አቅጣጫዎች ተስለው የሚገኙና እነዚህን መነሻ አድርገው የተሳሉና የተቀረጹ ስራዎችም ሌሎች አስረጅዎች ናቸው፡፡

ይህ የ“Athropomorphism” አቀራረብ ለሥነ ምህዳር ጥበቃ ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሚጫወት በተለያዩ ጸሐፍት ሥራዎች ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ **ለምሳሌ** Ingold (2000: 90-91) “anthropomorphism”ን አስመልክተው እንደሚያስረዱት በዚህ ስልት የሚቀርቡ ትረካዎች በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ የተፈጠሩና እውነተኛ ገጠመኞችን መነሻ ያደረጉ፣ ሰዎች የሚኖሩበትን መልክዓምድር፣ በአካባቢያቸው የሚገኙ እጽዋትን፣ እንስሳትን፣ የአየር ጠባይን በጥልቀት ከመመልከትና መርምሮ ከመረዳት ይመነጫሉ፡፡ በሰዎችና በሌሎች ፍጡራን መካከል የሚኖር ተፈጥሯዊ ተመሳስሎን መሰረት በማድረግ፣ የሰው ልጆችን ልዩ ልዩ ባህርያት ሰው ላልሆኑ የተፈጥሮ ክፍሎች በመስጠት ይተረካሉ፡፡ በትረካዎች ውስጥ የሰውን ባህርያት ተላብሰው የሚቀርቡ ገጸባህርያት የሰዎች አምሳያዎች (metonymic- the animal is an extension of the human) ወይም ሰዎችን የሚተኩ ትእምርቶች (metaphoric- the animal substitutes for the human) ሆነው ነው፡፡ አያይዘውም በትረካዎች ውስጥ ሰዎች ወደ ሌላ ፍጥረት ወይም በተቃራኒው ሌሎች ፍጥረታት ወደ ሰው የሚያደርጉት ለውጥ በእውኑ ዓለም እንደማይተገበር (ከአስማተኞች በስተቀር) ገልጸዋል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ለውጡ አንዳንድ ጊዜ የባህርይ ብቻ አይሆንም፤ ሙሉ ወይም ከፊል አካላዊ ወይም የነፍስ ለውጥ፣ የአካልና የነፍስ ሙሉ ለውጥ ወይም ወደ መናፍስትነት መለወጥን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ፍጡራን በተረኮች ውስጥ ሟች አይደሉም፤ ዘለዓለማዊ ናቸው፡፡ እነዚህ ፍጡራን ከሞት በኋላ መንፈሳቸው ወደ ዛፍ፣ ውሃ፣ እንስሳ፣ ወዘተ. ይለወጣል ወይም በእነዚህ ፍጡራን ላይ መንፈሶቻቸው

ይሰፍራሉ ተብሎ ስለሚታመን የሰፈሩባቸው ወይም የተለወጡት አካላት በህይወት ባሉት እንዲፈሩ፣ እንዲከበሩ ታላቅ ኃይል (power) ይሰጣቸዋል፡፡ በየትኛውም መልክ ቢቀርቡ እነዚህ የትረካ ስልቶች ሰዎች ከተፈጥሮ ጋር ጥብቅ ትስስር እንዲኖራቸው ማድረጋቸው አያጠያይቅም በማለት አብራርተዋል፡፡

ወደዘጌ ሥነ ምህዳር አጠባበቅና አጠቃቀም ልማድ ስንመለስ፣ በዘጌ ከፍ ብሎ ከተገለጸው የአቡነ በትረማርያም በትር መንጭተዋል ተብሎ የሚታመንባቸው ሃይማኖትን፣ ባህልንና ሥነ ምህዳርን በእጅጉ ያቆራኙ ጉዳዮች በተለያዩ ትእምርቶች ተወክለው እናገኛለን፡፡ እነዚህ ትእምርቶች የተለያዩ ገጽታዎች አሏቸው፡፡ አንዱ ገጽታቸው ስእል መሳልና ቅርጻቅርጽ መስራት በምድር በረከት፣ በሰማይ ጽድቅ የሚያስገኙ ሙያዎች ተደርገው እንዲቆጠሩ የቆመ ነው፡፡ ሌላው ገጽታቸው ደግሞ ዘጌን በገነት በመመሰል፣ ሕይወት ያላቸውን ፍጥረታት (በዋናነት እጽዋትን) የጽድቅና የኩነኔ ተምሳሌት በማድረግና በአፈጣጠር ባሕርይ ከሰው ጋር በማዛመድ የተለየ አካባቢያዊ የአምልኮ ሥርዓት በመገንባት የቀረበ ሲሆን፣ ይህንን ሥርዓት ለማስጠበቅ እንደ መቅሰፍተ እግዚአብሔር የሚቆጠሩ መብረቅን፣ ነብርን፣ እባብን፣ ዘንዶንና ሌሎችንም መከራዎች በቅጣትነት በማቆም ተገልጿል፡፡ በረከቶችን በመሻት፣ ቅጣቶችን በመፍራት መካከል (Equilbrum) የተፈጥሮ ሚዛን ተጠብቋል፡፡ እንስሳት የማይገደሉበት፣ ደን የማይመነጠርበት፣ የሰብል እርሻ የማይተገበርበት የዘጌ ተፈጥሯዊ አካባቢ (ሥነ ምህዳር)፣ እና የተለየ ዘገኛ ማንነት ተመስርቷል፡፡ እነዚህ በረከቶችና ቅጣቶች የቀረቡባቸው የአመሳሰል (representation) ሥርዓቶች በግልጽ ይታያሉ፡፡ በረከቶችና ቅጣቶች ደግሞ በበኩላቸው ፍጥረታት ከበረከት ተቆጥረው እንዲከበሩ ወይም እንዲፈሩ የሚያደርግ የተለየ ሃይማኖታዊ ማንነት በመገንባት የዘጌ ማኅበረሰብ ለተፈጥሮ ስሱ (nature - sensitive)፣ ተፈጥሮን ጠባቂ (nature - protective)፣ እና ከተፈጥሮ ጋር ወዳጅ ወይም ተፈጥሮን አፍቃሪ (nature - friendly) በማድረግ፣ የአካባቢው ማኅበረሰብና ተፈጥሮ ለረጅም ዘመናት ተናብበው እንዲኖሩ ያስቻለ ሥነ ምህዳራዊ ማንነትንና ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ሌሎች ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና ሳይንሳዊ ጥቅሞችን አስገኝቷል፡፡

በቃል፣ በስእልና በቅርጻቅርጽ በቀረቡ ተረኮች ውስጥ ከተገለጹ ጉዳዮች ውስጥ "በዚች ቦታ እርሻ፣ ቁፋሮ መሆን የለበትም፤ በደን የተሸፈነች ገነት መሰል ገዳም መሆን አለባት" የሚለው አንዱ ነው፡፡ ይኸው ገለጻ ስለ ገነት እንድናስብ ይመራል፡፡

ገነት አራት ወንዞች ማለትም ግዮን ወተት፣ ኤፍራጥስ ዘይት፣ ኤፌሶን ወይን፣ ጤግሮስ ማር ሆነው እንደ መስቀል ተመሰቃቅለው

የሚያጠፏት፣ ለምለም ሥፍራ ናት (ዘፍ. 2፥ 11-15)። በዚህች ሥፍራ አሳዳጅና ተሳዳጅ ሳይኖር ሁሉም ፍጥረታት በኅብረት ይኖራሉ ተብሎ እንደሚታመነው፣ ዘጌም የገነት አምሳል ነው ተብሎ ስለሚታመን በሥፍራው የሚገኝ ፍጥረት ሁሉ ይከበራል። መከበር እንዳለበትም በሃይማኖት አባቶች ይመከራል፤ ይዘከራል። ይህም የሚሆነው ስለእያንዳንዱ ፍጥረት ሃይማኖታዊ ተምሳሌትነት በማስረዳት፣ የዘጌን ገነትነት በማጉላት ነው። እጽዋትን በምሳሌነት እንመልከት።

"በገነት ውስጥ ያሉ አዝእርት፣ አትክልት፣ እጽዋት፣ ፍሬያቸው ክብ ነው። ፍሬያቸውን ማን ይመገበዋል ቢሉ ብሔረ ብፁአን ያሉ ጻድቃን፣ ቅዱሳን፣ በገነት ያሉ አእዋፍ ይመገቧቸዋል። ገነትን ለማናፈስ የተሾመው ነፋስ ዘወትር በዘጠኝ ሰዓት ወደ ምስራቅ አሻቅቦ ሲነፍስ ፍሬውን እንደ ዝናብ ይጥልላቸዋል፤ ያንን እየተመገቡ ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ ይኖራሉ" (ማቴ. 13፥ 8-10)።

በዘጌ የሚገኙ እጽዋት ደግሞ (እነዚህ እጽዋት መገኛቸው በዘጌ ብቻ የተወሰነ አይደለም) የአብዛኞቹ ፍሬ ክብ ነው። ለምሳሌ የዋንዛ፣ የሾላ፣ የዋርካ፣ የአጋም፣ የቀጋ፣ የእሸ፣ የችብሃ፣ የቡና። ሥፍራው ከግዮን የሚጠጣ፣ ነዋሪዎችና በሥፍራው የሚኖሩ ፍጥረታት ደግሞ ፍሬውን እየበሉ፣ ውሃውን እየጠጡ፣ ፈጣሪን እያመሰገኑ የሚኖሩበት ሥፍራ፣ አምሳለ ገነት ነው ብለው እንደሚያምኑ አባ ገብረሥላሴ ይገልጻሉ (ቃለመጠይቅ፣ 16/7/2011 ዓ.ም)።

ሥፍራውን በገነት ከመመሰል በተጨማሪ የእጽዋቱን፣ የእንስሳቱንና የአእዋፍን ተፈጥሮ በጻድቃንና በኃጥአን እየመሰሉ፣ ከሰው ባህርያት ጋር እያስተሳሰሩ ማቅረብ ሌላው ብልሃት ነው።

> እጽዋቱና አዝእርቱ በራሳቸው የሚያፈሩ (እነዚህ በእርሻቸው ጥረው ግረው የሚኖሩ ተምሳሌቶች ናቸው)፣ በጎናቸው የሚያፈሩ (እነዚህ ነግደው የሚኖሩ ተምሳሌቶች ናቸው)፣ በስራቸው የሚያፈሩ (እነዚህ በሰራተኛ፣ በሎሌ የሚያሰሩ ተምሳሌቶች ናቸው) አሉ። በራሳቸው፣ በጎናቸው፣ በስራቸው አፍርተው ፍሬያቸውን ወፍ ጠርጥሮት፣ ጠላት ለቅሞት የሚቀሩ አሉ። በስራቸው አፍርተው ፍሬያቸውን ከጠላት ሸሽገው የሚያስቀሩ አሉ። እነዚህም ምሳሌዎች ናቸው። በራሳቸው የሚያፈሩት በዚህ ዓለም ብዙ ትሩፋት ሰርተው ይዩልን፣ ይስሙልን፣ ይወቁልን ብለው በከንቱ ውዳሴ ተጎድተው በወዲያኛው ዓለም ሳይጠቀሙ የሚቀሩት አምሳል ናቸው። ሸሽገው የሚያስቀሩት ደግሞ የእነዚያ ተቃራኒዎች ናቸው። በሌላ በኩል ሁሉም ከአንድ መሬት ተፈጥረው አንዱ ወገን ጣፋጭ፣ ሌላው ወገን ሬትና መርዝ ናቸው። እነዚህም ጣፋጭ የሚያፈሩ የጻድቃን፣ ሬትና መርዝ

> የሚያፈሩ የኃጥአን አምሳል ናቸው፡፡ እጽዋት ከአንድ መሬት በቅለው በመጣፈጥና በመምረር እንዲለዩ ሁሉ ጻድቃንና ኃጥአንም ከአራቱ ባሕርያት ተፈጥረው በምግባርና በሃይማኖት፣ በክህደትና በኃጢአት፣ በክፋትና በበጎነት ተለይተው ሲኖሩ ጻድቃን ምግባር ሰርተው፣ ሃይማኖት አጽንተው ሲኖሩ ወደ መንግስተ ሰማያት ይገባሉ፡፡ ኃጥአንም በክህደት፣ በኃጢአት፣ በክፋት ጸንተው ሃይማኖት አፍርሰው ሲኖሩ ወደ ገሃነመ እሳት ይወርዳሉ (ሠናይ 2009፡ 82)፡፡

የእጽዋት ሃይማኖታዊ ተምሳሌትነት በፍሬያቸው ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ የሚለመልሙበት፣ የሚያብቡበትና የሚያፈሩበት ወቅት ሁሉ ተምሳሌትነት አለው፡፡ ክረምት ከበጋ ለምልመው፣ አብበውና አፍርተው የሚኖሩት የጻድቃን አምሳል፣ እንደነማን ቢሉ እንደ አብርሃም፣ እንደ ይስሐቅና እንደ ያዕቆብ፡፡ በዚህ ዓለም ሳሉ ወልደው፣ ከብደው፣ ገዝተው፣ ነድተው፣ በልተው፣ ጠጥተው፣ በወዲያኛው ዓለም ተጠቅመው፤ የጻድቃን ነፍስ ሁሉ ስትሄድ "በአብርሃም፣ በይስሐቅና በያዕቆብ እቅፍ አስቀምጥልን" ሲባሉ ይኖራሉ (ዝኒከማሁ 2009፡ 88)፡፡

በዘጌ ከሚገኙ ተክሎች ውስጥ እሸ፣ ሰሳ፣ ክነዳባ/ክደን አባና ደንገል ዓመቱን ሙሉ ለምለም ናቸው፡፡ በጫፋቸው፣ በስራቸው፣ በጎናቸው የሚጠለለው ፍጥረት ብዙ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ የሰሳና የክደን አባ ዛፎች፡፡ የአካባቢው ማኅበረሰብ የሰሳ ዛፍን አባት ሰሳ፣ እናት ሰሳ፣ ክነዳባን ደግሞ አባ ክደን (አባ አልብስ) እያሉ መጥራታቸው ሲታይ ከተምሳሌቱ ጋር ይሰምራል፡፡

ከተጠቀሱት እጽዋት ደንገልን በምሳሌነት በማንሳት የሚሰጣቸውን ማኅበራዊና ሥነ ምህዳራዊ ፋይዳዎችን በዝርዝር እንመልከት፡፡


ደንገል በጣና ሃይቅ ዳርቻና ዙሪያ ገባውን ከብቦ በሚገኝ ረግረጋማ ሥፍራ ሁሉ በብዛት የሚገኝ፣ ዓመቱን ሙሉ አረንጓዴ ወይም ለምለም ሆኖ የሚኖር ተክል ነው፡፡ ይህ ተክል አይረባም ተብሎ የሚጣል ክፍል የሌለውና በማኅበረሰቡ አጠቃላይ ማኅበረ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት ውስጥ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ተክል ነው፡፡ እንደ አቶ ዳንኤል አገላለጽ ጫፉ ቄጤማ (ጨፌ) ነው፤ ለቡና ሥርዓት፣ ለጽዋና ለሌሎች የድግስ ዓይነቶች የቤት ማሳመሪያ (ጉዝጓዝ) ይሆናል፡፡ እንዲህም ስለሆነ ከዚሁ ተክል የሚገኘው ቄጤማ ከራስ ፍጆታ አልፎ የቄጤማ አቅራቢና ቸርቻሪ በመሆን ለተሰማሩ የአካባቢው ተወላጆች የሥራ እድል ሆኗል፤ ኑሯቸውንም እንዲደጉሙ እድል ፈጥሯል (ቃለመጠይቅ፣ 21/6/2011)፡፡

የደንገል ግንዱ የባህላዊ ቤቶች፣ የባህል ዘመናዊ መዝናኛዎች (lodges)፣ ለቤተ ክርስቲያን ጣሪያና ግድግዳ ክዳን ይሆናል፡፡ ለወለልና ለመደብ

የሚሆን ምንጣፍ ይሰራበታል፡፡ ለባህላዊ ታንኳ፣ ለስፌት በተለይም በዚህ ዘርፍ በቋሚነት የሚተዳደሩ የነገደ ወይጦ ማኅበረሰብ አባላት ደንገልን እንደ ሰበዝም እንደ መስፈያ (አክርማ) ይጠቀሙበታል፡፡ ለጎብኝዎች የሚዘጋጁ የስጦታ እቃዎች (ትንንሽ ታንኳዎች) ይሰራበታል፡፡ ደንገል ለእንስሳት መኖ ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ የተረፈው የደንገል ክፍል ደግሞ ማገዶ ይሆናል፡፡

ስለ ደንገል ከፍ ብሎ ከተጠቀሰው አገልግሎቶቹ በተጨማሪ ሥነ ምህዳራዊ ጠቀሜታው ጉልህ ነው፡፡ ወረቤ የተባሉ የአእዋፍ ዝርያዎች በዚህ ተክል ጫፍ ላይ የሚገኘውን ቁጤማ በመጠቀም በተክሉ ላይ ጎጇቸውን ይሰራሉ፡፡ ሌሎች ወፎች እንደ ስንዝሬት፣ ጋጋኖ፣ ማንካ አፍ፣ ዝይ፣ ዳክየ፣ ወዘተ. ይኖሩበታል፤ ይራቡበታል፡፡ እነዚህ አእዋፍ በሚራቡበት ወቅት አእዋፉ ለመራቢያነት የመረጡት አካባቢ የሚገኝ የደንገል ማሳ እንዳይታጨድ በአካባቢው ሽማግሌዎች፣ በደንና የተፈጥሮ ሃብት ባለሙያዎች ይከለከላል፡፡ ደንገል በባህርይው የጣና ሃይቅንና የአባይ ወንዝን ተከትሎ በከበበ ረግረግ ሥፍራ ሁሉ ስለሚገኝ ወደ ሃይቁም ይሁን ወደ ወንዙ ጎርፍ በሚገባበት ጊዜ አፈሩን በስሩ አስቀርቶ የተጣራ ውሃ እንዲያልፍ በማድረግ በደለል ከመሞላት ይታደጋቸዋል፡፡ ከሆቴሎችና ከሌሎች ተቋማት የሚለቀቅ ፈሳሽ ቆሻሻን በስሮቹ በመምጠጥ ወይም ስርገትን በመከላከል ብክለትን ይቀንሳል፡፡ በአንጻሩ እነዚህ ቆሻሻዎች ለደንገሉ ምቹ ምግቦች ናቸው፡፡ ወደ ሃይቁ የሚጣሉ የማይበሰብሱ ነገሮችን እንደ ፌስታል፣ የመጠጥና የምግብ ፕላስቲኮችን እንዳይገቡ ይከላከላል፡፡ እነዚህን ነገሮች በስሩ ስለሚይዛቸው ጎርፍ የሚያመጣው ደለልና ከተለያዩ ተቋማት የሚመጣው ፈሳሽ ቆሻሻ ያርፉባቸውና በራሳቸው ጥሩ እርከን በመስራት ደንገሉ የሚራባበት ምቹ እድል ይፈጥሩለታል፡፡ ከዚህ ሌላ ደንገል ስሮቹ ዓሳዎች ከሃይቁ በመውጣት እንቁላሎቻቸውን በመጣል፣ ፈልፍለው ያሳድጉበታል፡፡ የአባይ ወንዝ አዞዎችና ዘንዶም እንዲሁ ታዳኝ እንስሳትን አድፍጠው የሚያጠምዱበት፣ ጉማሬዎች የሚወልዱበትና ወጥተው ፀሐይ የሚሞቁበት ምቹ የመኖሪያ ሥፍራ ነው (አቶ ዳንኤል፣ ቃለመጠይቅ፣ 21/6/2011 እና ዶ/ር አያሌው ቃለመጠይቅ፣ 19/7/2011)፡፡

ፎቶግራፍ ቁጥር 2፣3፣4፣5፡- የደንገል ተክልና አገልግሎቶቹ በጥቂቱ




ምንጭ፡- በመስክ ስራ ወቅት በተመራማሪው የተነሱ

ደንገል በጣና ሃይቅ ላይ የተከሰተውን መጤ አረም (እምቦጭ) ለማጥፋት ተሞክሮ ጥሩ ውጤት በማስገኘቱና ተክሉ የሚሰጠው ጠቅላላ አገልግሎት ግምት ውስጥ ገብቶ በአሁኑ ወቅት ይህንን ተክል መልሶ ለማልማት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና የማኅበረሰብ አገልግሎት በጣና ሃይቅ፣ የባሕር ዳር ከተማን አቋርጠው በሚያልፉ ትንንሽ ወንዞች፣ በቆጋ፣ በግልገል በለስና በደቡብ ጎንደር በሚገኙ ረግረጋማ ሥፍራዎች ትልቅ ፕሮጀክት አድርጎ እየሰራበት እንደሚገኝ የደንገል ልማት ፕሮጀክት ኃላፊ የሆኑት ዶክተር ንብረት ገልጸውልኛል (ቃለመጠይቅ፣ 18/7/2011)፡፡

ከዚህም ሌላ እጽዋትን፣ እንስሳትን፣ አእዋፍን፣ በአፈጣጠር ባሕርይ ማለትም በባሕርያተ ስጋ (እሳት፣ ነፋስ፣ ውሃ፣ መሬት) ከሰው ጋር ሠናይ (2009፡ 149-150) እንደሚከተለው ያስተሳስሯቸዋል፡፡

> አዳምን ከምን ሰራው ቢሉ ከመሬትና ከውሃ፣ ከእሳትና ከነፋስ፡፡ እሳትና ነፋስ ደመ ነፍስ፣ ሰው መሞትና መኖሩ በትንፋሹ፣ በሙቀቱ እንዲታወቅ፡፡ የውሃና የመሬት ግብራቸው እንዲህ ነው፡ ፡ የመሬት ግብሩ መወፈር ነው፡፡ ስጋ፣ ጅማት፣ ጸጉር፣ ጥፍር፣ ግዙፍ አካል የሚሆን መሬት ነው፡፡ የውሃ ግብሩ ደም፣ ምራቅ፣ እንባ፣ ሽንት ሆኖ የሚፈስ ነው፡፡ እንስሳት፣ አዝእርት፣ እጽዋት ይህንን ባሕርይ ይጋራሉ፡፡ ደመ ነፍስ አላቸው፡፡ ሁሉም በየግብሩ ይዋለዳል፡፡ በእሳትነታቸው እጽዋት እንጨት ለእንጨት ባሳበቋቸው ጊዜ እሳት ይወጣቸዋል፤ በውሃነታቸው በብረት ቢወጓቸው ደም፣ ውሃ፣ ወተት ይፈሳቸዋል፡፡ በመሬትነታቸው ያድጋሉ፤ ይገዝፋሉ፤ ይወፍራሉ፡፡ ተቆርጠው በወደቁም ጊዜ ይደርቃሉ፤ ይፈርሳሉ፤ አፈር ትቢያ ይሆናሉ፡፡

መሬት፣ እሳት፣ ውሃ፣ ነፋስ፣ ዝናብ፣ ክረምት፣ በጋ፣ ወዘተ. ሁሉ ሃይማኖታዊ ተምሳሌትነት አላቸው፡፡

በጥቅሉ "ዘጌ ገነት መምሰል አለባት" የሚለው አገላለጽ እጽዋትንና እንስሳትን የጽድቅ እና የኃጢአት ተምሳሌት በማድረግ ሃይማኖታዊ መሰረት በማስያዝ ፍጥረታቱ በማኅበረሰቡ እንዲከበሩ ወይም እንዲነወሩ የሚያደርግ ነው፡፡ እነዚህን ፍጥረታት የጽድቅና የኃጢአት ምሳሌ ማድረጋቸው ፍጥረታቱ ባሉበት እንዲከበሩ ወይም እንዲነወሩ ያደርጋል እንጅ እንዲነኩና እንዲወገዱ ግን ያበጁት ሥርዓት አይፈቅድም፡፡ "የአካባቢው ደን በተለይም ትልልቅ ዛፎች የመናፍስት ማደሪያዎች፣ የህቡአን አባቶች መኖሪያዎች ናቸው" የሚለው እምነት በአካባቢው መኖር በምሳሌነት ይነሳል፡፡

ትልልቅ ዛፎች በተለያዩ ምክንያቶች ይፈራሉ፤ ይከበራሉ፡፡ የአንዳንዶች ከሚሰጡት ዓለማዊና መንፈሳዊ አገልግሎት ጋር የተዛመደ ነው፡፡ ትልልቅ ዛፎች በባህርያቸው ለደከመ ጥላቸውን፣ ለተራበ ፍሬያቸውን ይሰጣሉ፤ ለሰው፣ ለእንስሳት፣ ለአእዋፍ፣ ለነፍሳት፣ ሁሉ፡፡ ከጥላቸው፣ ከግንዳቸው፣ ከቅርንጫፎቻቸው፣ ከቅጠሎቻቸው፣ ከስሮቻቸው የሚጠለለው፣ ምግቡን የሚፈልገው፣ ከጠላት ራሱን የሚደብቀው፣ ግዳዩን ለመጣል የሚጠብቀው ወይም የሚያደፍጠው ሁሉ መናኸሪያዎች ናቸው፡፡ ዋርካና ሾላ ይህ ባህርይ ይታይባቸዋል፤ ሁሉንም የማስጠጋት፡፡ በተለይም ፍሬ በሚያፈሩበት ወቅት እንስሳትና አእዋፍ ፍሬያቸውን ለመመገብ ወይም በዛፎቹ ለመጠለል እንዲሁም ፍሬ ለመብላት የሚመጡ ታዳኞቻቸውን ለማጥመድ (ሰውን ጨምሮ)

ይመርጧቸዋል። ሰብልን፣ የቤት እንስሳትን፣ ካልበረታም ራሱን ሰውን ጨምሮ ለማጥፋት የሚጣጣሩ አደገኛ እንስሳት (ለምሳሌ ነብር፣ እባብ፣ ዘንዶ) በቀንም ሆነ በማታ ወደ እጽዋቱ ይመጣሉ። የእጽዋቱን ፍሬ ለመብላት ደግሞ ሚዳቆ፣ ዝንጀሮ፣ አሳማ፣ ከርከሮ፣ ጦጣ፣ ፎጥ፣ የቤት እንስሳትም በተለይ የቀንድ ከብቶች ወደ እጽዋቱ ያመራሉ። በዚህ ጊዜ አዳኝ አራዊት ይዘው ይበሏቸዋል። አዳኝ ሰዎችም ዛፉ ላይ ሆነው ቅጠል ለብሰው በመጠበቅ ሲመጡ ይገድሏቸዋል።

"ተናዳፊና አደገኛ እንስሳት ሰዎችን በዚያ ሥፍራ ቢያገኙ በሶስት ምክንያቶች ሊያጠቁ ይችላሉ። እነዚህም ራሳቸውን ለመከላከል፣ ርቧቸው አማራጭ ሲያጡና በስሪያ ወቅቶች ናቸው። ስለሆነም ዛፎች የአዳኝና የታዳኝ ተራክቦ የሚካሄድባቸው ሥፍራዎች ናቸው። ይህም ሳይንሳዊ ነው" (አቶ ዳንኤል፣ ቃለመጠይቅ፣ 7/8/2011)።

በየባህሉ ትልልቅ ዛፎች መናፍስት ይኖሩባቸዋል፤ አትቅረቡ እየተባለ የሚመከረው ባንድ በኩል ይህንን አመላቸውን ማለትም ዛፎቹ የአደገኛ እንስሳት መገኛ መሆናቸውንና የእንስሳቱን ባህርይ ከመረዳት፣ በሌላ በኩል ትልልቅ ዛፎች ቢቆረጡ የሚደርሰውን ምድራዊ መናጋት ቀድሞ ከመረዳት የመነጨ ሊሆን እንደሚችል መረዳት ይቻላል።

ይህ "ትልልቅ ዛፎች መናፍስት ይኖሩባቸዋል" የሚለው እምነት በሌሎች ሕዝቦች ልማዶች ውስጥም ስለመኖሩ በቀደምት ጥናቶች ተነስቷል። ለምሳሌ Martin et al. (2011: 45) በሴራሊዮን ቅዱሳን መካናት ለአደን፣ ለውሃ ምንጭ መጎልበት፣ ለዓሳ ምርት፣ ለእፀ መድኃኒት ቅመማ ተግባር ስለሚጠቅሙ አይነኩም። የመናፍስት መኖርያዎች ናቸው ተብሎ ስለሚታመን ይከበራሉ፤ ይፈራሉ። እነዚህን ቅዱስ መካናት መንካት መናፍስቱን በማስቆጣት እንደ መብረቅ፣ ጎርፍ፣ ድርቅ፣ በቤት እንስሳትና በሰዎች ላይ መካንነት ይከሰታል፤ የተወለደው ይሞታል፤ የሰብል ምርት ይቀንሳል ተብሎ ይታመናል።

በኢትዮጵያ በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎችም የእስልምና እና የክርስትና ሃይማኖት ተቋማት የተፈጥሮ ሀብቶችን በመጠበቅ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ የገለጹ አሉ። ለምሳሌ በወሎ ሙስሊሞች "Wajjib" እንደ ቅዱስ የሚቆጠር ሥፍራ ነው። በዚሁ ሥፍራ የሚገኙ ዛፎች መስጅዶችን ለመስራትና ለመጠገን ካልሆነ በስተቀር አይቆረጡም (Teferi 2008: 15)።

በቱለማ ኦሮሞ ኦዳና ትልልቅ ዛፎች መታወቂያ ሆነው ያገለግላሉ። የአያት የቅድመ አያት የመቃብር ሥፍራዎች በመሆናቸው አይነኩም። የክበራ ማዕከልም ናቸው (ጥላሁን 2007፡ 188-189)።

በጉጂ ኦሮሞዎች ባህላዊ እምነት ውስጥ ደግሞ የ"Woyyu" ዛፍ ከገዳ ሥርዓት ከበራ ጋር የተያያዘ ነው። ይህንን ዛፍ እንደ የጋራ ሀብት ቆጥሮ የመንከባከብ ልማድ ስላለ ዛፉ ጉጂዎች በሚኖሩባቸው ቀየዎች ሁሉ በብዛት ይገኛል። በእነዚህ ዛፎች ስር ጉጂዎች እንደ ሸምግልና፣ ጋብቻ የመሳሰሉ ሥርዓቶችን ይከውናሉ። አረንጓዴ ዛፎችና ለምለም ሳር በአብዛኛው የኦሮሞ ህዝብ ልማድ ውስጥ የሰላምና "የማጎጸን ልምላሜ"/fertility/ ትእምርት ናቸው። አረንጓዴ አካባቢ የሕይወት ምንጭ/source of life/ ነው ተብሎ ይታመናል። በአብዛኛው የኦሮሞ ሕዝብ የእምነትና የታሪክ ሂደት ውስጥ በደጋው ክፍል የሾላ (fig)፣ በቆላው ደግሞ የግራር ዛፎች ጠንካራ ተምሳሌቶች በመሆናቸው እነዚህ ዛፎች አምልኮ በሚፈጸምባቸው ተራራዎችና ኮረብታዎች በብዛት ይገኛሉ። ጥበቃና እንክብካቤም ይደረግላቸዋል። ምክንያቱም እነዚህ ዛፎች ከመንፈሳዊ አገልግሎታቸው ሌላ የሕዝቡ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሃይማኖታዊ ችግሮች ለውይይት የሚቀርቡባቸው፣ የሚፈቱባቸው ስለሆነ ነው። በሁሉም የኦሮሞ ሕዝብ ባህልና እምነት ውስጥ ደግሞ "Dakki" ዛፍ የሰላምና የመረጋጋት፣ "Odda" የቅድስና ትእምርቶች ናቸው። ማንም ሰው እነዚህን ዛፎች እንዲነካ አይፈቀድለትም (Teferi 2008: 17-19፤ ጥላሁን 2007፡ 188-189)።

በዘጌም የትኛውንም ዛፍ ያለ አግባብ መቁረጥ አይፈቀድም። ዛፉም ሆነ የበቀለበት መሬት፣ በሥፍራው የሚኖሩ ፍጥረታት ሁሉ የቅዱሱ ሥፍራ፣ የዘጌ አካል ናቸው ተብሎ ይታመናል።

እንደ Martin et al. (2011: 45) አመዳደብ ሶስት ዓይነት ቅዱሳን መካናት (sacred groves) አሉ። እነዚህም የአያት፣ የቅድመ አያት መንፈሶች ይጠብቋቸዋል ተብሎ የሚታመንባቸው ደኖች (ancestral forests)፣ መካነ መቃብሮች (forest cemeteries)፣ እና አባሎቻቸው ብቻ እንዲገቡባቸው የሚፈቀዱ "የድብቅ/ምስጢራዊ ኅብረተሰቦች ደኖች" (forest of secret society) ናቸው::

የዘጌ ደን ከሶስቱም ጋር ተመሳሳይ ነው። ይኸውም "በዘጌ ደን ውስጥ ህቡአን ወይም ስውራን አባቶች ይኖራሉ፤ ደኑን መንካት እነዚህን አባቶች ያስቆጣል" ተብሎ መታመኑ አንዱ ነው። ሌላው ሥፍራው ቅዱሳን ኖረውበት ተአምራት የሰሩበት (ለዚህ አስተዋጽኦዋቸው ሲባል ተአምራት በፈጸሙበት ቦታ በስማቸው መታሰቢያ ቤተ ክርስቲያን የተቋቋመላቸው)፣ ከሃይማኖቱ ተከታይ በስተቀር በዘጌ ባሕረ ሰላጤ የሌላ ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ሰው እንዲኖር የማይፈቀዱ በመሆናቸው ነው። ገዳማቱና የአካባቢው ማኅበረሰብ የቅዱሳን መካናቱ (የደኑ፣ የአእዋፍና የእንስሳቱ፣ የሃይቁ፣ ወዘተ.) ባለቤቶች ናቸው።

እንዲህም ስለሆነ በዘጌ ማኅበረሰብ ማንኛውም ዛፍ ትልቅ ይሁን ትንሽ ያለ አግባብ አይቆረጥም፡፡ አቡነ በትረማርያም "ዘጌ ገነት ትሁን፤ ነዋሪዎች ጠቢባን ይሁኑ" ሲሉ መርቀዋል፤ አዘዋል፡፡ ዛፍ እንዳይቆረጥ፣ እንስሳት እንዳይገደሉ፣ እንስሳትም ሰውን እንዳይተናኮሉ ግዝት አድርገዋል፡፡ ነዋሪዎችም እነዚህን ግዝቶች ከተላለፍንና የአባታችንን ቃልኪዳን ካፈረስን መብረቅ ይመታናል፤ በደኑ ውስጥ የሚኖር ዘንዶ ይውጠናል፤ ነብር ይበላናል፤ እባብም ይነድፈናል ብለው ያምናሉ፡፡ ይህንን እምነት በመገንባት፣ ዛፍ እንዳይቆረጥ፣ እንስሳት እንዳይታደኑና የአካባቢው ሥነ ምህዳር እንዲጠበቅ ለማድረግ በቅጣትነት ከቆሙ ትእምርቶች መካከል ደግሞ መብረቅ፣ እባብ፣ ነብር፣ ዘንዶ ተጠቅሰዋል፡ ፡ ከተጠቀሱት የቅጣት ትእምርቶች ውስጥ መብረቅን በምሳሌነት እንመልከት፡፡

መብረቅ በባህርይው ከፍ ብሎ የሚገኝን ነገር ሁሉ ይመታል፤ በተለይም ትልልቅ ዛፎችን፡፡ ለዚህም ሲባል በመኖሪያ ቤት፣ በከብቶች ማደሪያና በስራ ማዘውተሪያ አጠገብ የሚገኝ ትልቅ ዛፍን መቁረጥ ልማድ ነው፡፡

መብረቅ መጠኑና መልኩ የማይታወቅ፣ የማይጨበጥና ረቂቅ ነገር ቢሆንም በዘጌ ማኅበረሰብ ልማድ ውስጥ ግን መብረቅ መልክ ተሰጥቶት፣ ቅርጽ ወጥቶለት፣ ተጨባጭ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህ ስለመብረቅ ያለ ማኅበራዊ አተያይ የተገነባው ደግሞ አንድም ከዚህ ቀደም እንዳየነው በቃል፣ ሌላም በስእልና በቅርጻቅርጽ አማካይነት ነው፡፡

በስእልና በቅርጻቅርጽ እንደተገለጸው በአካባቢው ማኅበረሰብ አመለካከት መብረቅ የቀይ አውራ ዶሮ መልክ ያለው፣ ከላዩ ላይ መልአክ ሞትን የተሸከመ፣ የቁጣና የቅጣት መልአክ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ የቁጣ መልአክ ወይም መብረቅ ተረኮችን መነሻ አድርገው በተሳሉ የግድግዳ፣ የብራና እና የገበታ ስእሎች እንዲሁም ቅርጻቅርጾች አማካይነት ተደጋግሞ ቀርቦ እናገኘዋለን፡፡

**ፎቶግራፍ ቁጥር 6፡- መብረቅ**



ምንጭ፡- በመስክ ስራ ወቅት በተመራማሪው የተነሳ

ከላይ እንደተገለጸው በረከቶችና ቅጣቶች በተለያዩ መንገዶች እየቀረቡ የዘጌ ማኅበረሰብ ከሥነ ምህዳር ጋር ያለው መስተጋብር ጤነኛ እንዲሆን ያስቻሉ ሌሎች ሥርዓቶችን አስገኝተዋል። በዚህ ረገድ ጥሩ ማሳያ የሚሆነን ለቡና የተሰጠ ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ አተያይ ነው። ቡና በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በከፋ አካባቢ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደተገኘና ከተገኘበት አካባቢ ከፋ "coffee" የሚለውን መጠሪያ እንዳገኘ ይነገራል። አገሪቱ ለውጭ ገበያ ከምትልካቸው ምርቶች ውስጥ ከፍተኛውን ደረጃ የሚይዝም ነው (ይሁኔ 2010፡ 251)።

ይሁን እንጅ በአንዳንድ አካባቢዎች ቡናን መጠቀም የክርስትና ሃይማኖት ሥነ ምግባርን እንደመጣስ ተቆጥሮ በቡና አጠቃቀም ላይ የተለያየ ማኅበራዊ አተያይ እንዲኖር አድርጓል። ቡና ጥቅም ላይ እንዳይውል የሚከለክሉ አካላት የሚያቀርቧቸው ምክንያቶች ቡና ሱስ አስያዥ በመሆኑ ጾም ያስፈታል፤ ሲወቀጥም ሆነ ሲደቆስ በዓልን ያስሽራል፤ ሰውን ለሀሜት ይጋብዛል፤ ለባእድ አምልኮ ተግባር ይውላል የሚሉ ናቸው። እነዚህ የክርስትና ሃይማኖት ተጻራሪ ተግባራት በሃይማኖቱ ተከታዮች እንዳይፈጸሙ ሲባል "ቡና፣ ትምባሆና ጫት ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለ ጊዜ እጽዋት ሲጠወልጉ እነዚህ እጽዋት ለምልመዋል፤ የበቀሉትም ከሰይጣን ሽንት ላይ ነው" በማለት፣ ቡናንም "የቆላ፣ ያፈላ፣ የጠጣ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም" እያሉ ሃይማኖታዊ መሰረት ሊሰጡ ሲጥሩና የክርስትና ትምህርት አካል አድርገው ሲሰብኩ ይሰማል (መጋቢ ሀዲስ ሰማኸኝ፣ ቃለመጠይቅ፣ 12/8/2011)።

እነዚህ ስብከቶች የቡና ተክል ላይም ሆነ ምርትና አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደራቸው አይቀርም።

በዘጌ ማኅበረሰብ ይህ አመለካከት የለም፡፡ ይህንን ሀሳብ በተመለከተ መጋቢ ሀዲስ ሰማኸኝ "ቡና በቀዳሚ ተረክበት በኢትዮጵያ ሀገር ወረከባ አሐዱ ኖላዊ አጣሊ ዘስሙ ካልድ ወስበ ርእያ ካልድ እንዘ ይበልዓ ጣሊ ውእቱኒ በልዓ እምፍሬሃ ወኮነ ንቀሃ አእምሮ፡፡ ወወሲዶ ወሀቦ ፩ መነኮስ ወተመጠዎ ውእቱ መነኮስ በልዓ እምፍሬሃ ወኮነ ንቁሃ ለጸሎት" የሚል ታሪክ እንደሚያውቁና ትርጉሙም "የቡና ምንጭ ኢትዮጵያ ናት፡፡ ካልድ የተባለ እረኛ ፍየሎቹ የቀላ የቡና ፍሬ ሲበሉ አስተዋለ፡፡ ፍየሎቹ ፍሬውን ከበሉ በኋላ ቀኑን በሙሉ ንቁ ሆነው ሲፈነጥዙ መዋላቸውን ተመለከተ፡፡ እሱም ከፍሬው ለቅሞ በላ፤ በብዙም ተነቃቃ፡፡ ይህንን ፍሬ ከበላ በኋላ እንደተነቃቃ በቅርብ ለነበሩ የገዳም መነኮሳት ነገራቸው፡፡ መነኮሳቱም ፍሬውን ለቅመው በበሉ ጊዜ ሌሊቱን ሁሉ ነቅተው በጸሎት ሲተጉ አደሩ" የሚል እንደሆነና ፍሬውን እየለቀሙ መቁላትና ማፍላትም ከገዳማት የተጀመረ ስለመሆኑ፣ ይህንን ተግባር ከገዳማት ውጭ የሚኖረው ኅብረተሰብ እየቀየ ለምዶት፣ ይህንኑ ልምድ ለንግድ ወደ ኢትዮጵያ ይመላለሱ የነበሩ ዓረቦች ለዓለም እንዳስተዋወቁት ነግረውኛል (ቃለመጠይቅ፣ 12/8/2011)፡፡

ከቀረበው ገለጻ እንደምንረዳው ቡናን ያገኙ ፍየሎች ናቸው፡፡ ፍየሎችን ያስተዋለ እረኛቸው ካልድ ነው፡፡ ለቅመው፣ ቆልተውና አፍልተው መጠጣትን የጀመሩና ያስፋፉ ደግሞ መነኮሳት ናቸው፡፡

በዘጌ ግን ይህ ሁኔታ የተለየ ነው፡፡ በተረኮች ውስጥ እንደተመለከተው "ቡና ለዘጌ አካባቢ ነዋሪ መጠቀሚያነት ከፈጣሪ የተሰጠ ጸጋ ነው" ተብሎ ስለሚታመን በብዛት ይመረታል፡፡ ምርቱ ለገበያ ይቀርባል፤ በመነኮሳቱም በአካባቢው ነዋሪም ይጠጣል፡፡ የአካባቢው ማኅበረሰብ ቡና አታምርቱ፤ ቡና አትጠጡ እየተባለ በገዳማቱ አባቶች አይሰበክም፡፡

ይህ አዎንታዊ አመለካከት በመኖሩ ምክንያት "1304.31 ሄክታር ከሆነው የዘጌ አጠቃላይ የቆዳ ስፋት ቡና 1016 ሄክታር ይሸፍናል፡፡ በሁሉም የዘጌ ቀበሌዎች በቡና ምርት ተጠቃሚ የሆነው የማኅበረሰብ ክፍል ወንድ 1381፣ ሴት 2487 በድምሩ 3868 አባወራና እማወራ ናቸው" በማለት የዑራ ቀበሌ አስተዳዳር ኃላፊ አቶ በሪሁን ነግረውኛል (ቃለመጠይቅ፣ 12/8/2011)፡፡

## ከሥነ ምህዳር ጥበቃና አጠቃቀም ጋር ተያይዘው እየተከሰቱ ያሉ ችግሮች

የአካባቢው ማኅበረሰብ መለያ ሆኖ የኖረው ዛፍ የመንከባከብ ባህል ከቡና ምርት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው፡፡ የቡና ምርት በድርቅና መሰል ችግሮች ምክንያት በተደጋጋሚ እየተፈተነ ይገኛል፡፡ የቡና ምርት መቀነስና የመስኖ አለመስፋፋት ደግሞ ማኅበረሰቡን በተለመደው

*መንገድ አምርቶ ራስን የመመገብ አቅም አሳጥቶታል፡፡ ስለሆነም ማኅበረሰቡ ከሥነ ምህዳር አጠባበቅ ጋር የተያያዙ የገዳማቱን የቆዩ ሥርዓቶች በማፍረስና ነባር ባህላዊ እሴቶችን በመጣስ ህልውናውን ለማሰንበት ያስችላሉ ያላቸውን ምርቶች ወደ ማምረት እየተሸጋገረ ነው፡ ፡ ለምሳሌ ዘጌ ከሌላው አካባቢ በሚዋሰንባቸው አካባቢዎች በተለይም በይጋንዳና አፋፍ አካባቢዎች ባሕር ዛፍና ጫት እየተተከሉ ነው፡፡ በእነዚህ ችግሮች ሳቢያ ተከብረው የኖሩ እሴቶች እየተናዱ፣ በድብቅ ለማገዶ፣ ለጣውላ ምርትና ለግንባታ ተግባር ዛፍ መቁረጥ ተጀምሯል፡፡*

**ፎቶግራፍ ቁጥር 7፡- በአካባቢው የሚካሄደውን የደን ምንጠራ የሚያሳይ**



ምንጭ፡- በመስክ ስራ ወቅት በተመራማሪው የተነሳ

እነዚህ ችግሮች መኖራቸው በአካባቢ ሥነ ምህዳር ጥበቃና ነባር ማኅበራዊ እሴቶች ላይ የሚያሳድሩት ጫና ቀላል አይደለም፡፡ ይኸውም ነባር ማኅበራዊ እሴቶችን የሚቃረኑ ተግባራት በአካባቢው እንዲጀመሩና እንዲስፋፉ በር በመክፈት በአባላቱ መካከል ጥቅምን መሰረት ያደረጉ

ግጭቶች እንዲከሰቱ፣ ተጠብቆ የኖረው ደን ለእርሻ፣ ለግንባታ፣ ለኃይል ምንጭ፣ ለግጦሽ ሲባል እንዲመነጠር፣ አደን እንዲስፋፋ፣ እነዚህም በጥቅሉ ሥርዓተ ምህዳሩ እንዲዛባ የሚያደርጉ ተግባራት ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በዘጌ የሚሰሩ ስእሎችና ቅርጻቅርጾች ገዳማቱንና ገዳማውያንን ከአካባቢው ማኅበረሰብና ከሥነ ምህዳር ጋር ያገናኛሉ፡፡ ይኸውም ልማዶቹ የማኅበረሰቡ አጠቃላይ ማንነት ከገዳማቱ አስተምህሮት ጋር በእጅጉ ተቆራኝቶ ለዘመናት በመዝለቅ፣ አሁንም ድረስ የአካባቢው ማኅበረሰብ ከገዳማት፣ ገዳማቱም ከአካባቢው ማኅበረሰብ፣ እንዲሁም ከሥነ ምህዳር ጋር እንዲተሳሰሩ አድርገዋል፡፡ ገዳማቱም መነኮሳት ለሰማያዊ ህይወት ብቻ የሚዘጋጁባቸው ሥፍራዎች አልነበሩም፤ አሁንም አይደሉም፡፡ ዓለማዊ ኑሮ የሚኖሩባቸው፣ መንፈሳዊና ዓለማዊ ትረካዎችን ወደ ስእልና ቅርጻቅርጽ የሚቀይሩባቸው፣ ስእል የመሳልና ቅርጻቅርጽ የመቅረጽ ባህላዊ እውቀታቸውን የሚያስተምሩባቸው፣ ልማዶቹ ከገዳማውያን ድንበር ተሻግረው ማኅበረሰቡ ጋር በመድረስ በሥነ ምህዳሩ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሌላቸው ሙያዎች በመሆን ቀስ በቀስ የአካባቢው ማኅበረሰብ ማንነት መገንቢያ፣ መትከያና ማስቀጠያ እንዲሆኑ የረዱ ተቋማት ናቸው፡፡

## Declarations

### Conflict of interst

The author declare that there is no conflict of interst

### Funding

The author received financial support from AAU.

## ዋቢ ድርሳናት

*መሪማ መሀመድ* (2009)፤ “የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነምሕረት ገዳም አመሰራረትና በገዳሚ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ትንተና”፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር፣ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የማስተርስ ዲግሪ ለማሟላት የቀረበ፡፡

ምህረት ተስፋዬ (2003)፤ "ከጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና

ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር፣ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የማስተርስ ዲግሪ ለማሟላት የቀረበ።

ሞገስ ሚካኤል (2007)፤ "በዘጌ ባህረ ገብ መሬት ላይ በሚገኙ ገዳማት ውስጥ የተሳሉ ጥንታዊ የግድግዳ ላይ ስእሎችና የአሳሳል ልማድ"፤ የአማርኛ ቋንቋና የባህል ዘርፎች ፫ኛው አገር አቀፍ ዐውደ ጥናት መድበል፣ ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት፣ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ፣ ፖሊ ሜዳ ማተሚያ ቤት።

ሞገስ ጀንበር (2003)፤ "ከዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችና አምልኳዊ ስርዓቶች"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር፣ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የማስተርስ ዲግሪ ለማሟላት የቀረበ።

ሠናይ ምስክር (2009)፤ መጽሐፈ አክሲማሮስ ዘቅዱስ ኤጲፋንዮስ፤ ዘስድስቱ ዕለታት ንባቡና ትርጓሜው፤ ባሕር ዳር፣ አፍሪካ አታሚ።

ብርሃኑ ገበየሁ (1999)፤ የአማርኛ ስነ ግጥም፤ አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚ ድርጅት።

ንጉሡ አክሊሉ (2004)፤ "የአየር ንብረት ለውጥ በኢትዮጵያ፤ መገለጫዎች፣ መዘዞችና ስጋቶች"፤ የአየር ንብረት ለውጥ፤ የአካባቢ ጥበቃና የዘላቂ ልማት ትስስር በኢትዮጵያ፤ አዲስ አበባ፣ በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ጥናቶች፣ ገጽ 1-20።

አስቴር ሙሉ (2000)፤ "ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በዘጌ ባሕረ ሰላጤ"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ በየኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የማስተርስ ዲግሪ ከፊል ማሟያ።

አንተነህ ደሴ (2001)፤ "በዳባት ገብርኤል ቤተመዘክር ውስጥ የሚገኙ ቁሳዊ ባህሎች መዘርዝር ከአጫጭር መግለጫ ጋር"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ የፎክሎር የመጀመሪያ ዲግሪ መርሃ ግብር፣ በፎክሎር የመጀመሪያ ዲግሪ ለማሟላት የቀረበ።

እሸቱ ጥሩነህ (2004)፤ "የስዕል ጥበብ ለባህልና ለልማት እድገት"፤ ባህልና ልማት በኢትዮጵያ፤ አዲስ አበባ፣ በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች፣ ገጽ 191-202።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (1948)፤ መጽሐፈ ሰዋስውበ ወ ግስ ወ መዝገበ ቃላት ሐዲስ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ወልደ አምላክ በውቀት (2004)፤ "የአየር ንብረት ለውጥን የድህነት ቁርኝት በኢትዮጵያ"፤ የአየር ንብረት ለውጥ፤ የአካባቢ ጥበቃና የዘላቂ ልማት ትስስር በኢትዮጵያ፤ አዲስ አበባ፣ በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ጥናቶች፣ ገጽ 21-36።

ወንድወሰን ሞላ (2007)፤ "በፃድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ጥናት"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የሂዩማኒቲስ፣

የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር፣ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤ (1980)፤ መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የሀዲስ ኪዳን መጻሕፍት፤ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ይሁኔ አየለ፤ (2010)፤ ሙሉ ጤናን ፍለጋ፤ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት።

ዮሴፍ ቦኪ፤ (2007)፤ "የደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተረኮች ጥናት ክዋኔ"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር፣ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ።

ጥላሁን ተሊላ፤ (2007)፤ "የቱለማ ኦሮሞ መርሣ (ሊሚናል) ወቅቶች ፎክሎር አውዳዊ ጥናት"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር የቀረበ የፒኤች ዲ ጥናት።

ፍሬህይወት ባዩ (2000)፤ "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገጽታ"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር፣ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የማስተርስ ዲግሪ ለማሟላት የቀረበ።

Abebaw, Ayalew. (2002). "A history of painting in east Gojjam in the eighteenth and nineteenth centuries: A study of the 'second Gondarine' style of painting" M.A.Thesis, Addis Ababa University, History Department.

Alemayehu, Wassie. (Year of Submission, undefined). "Opportunities, Constraints and Prospects of Ethiopian Orthodox Tewahido Churches in Conserving Forest Resources: The Case of Churches in South Gondar, Northern Ethiopia." Sweden, Swedish University of Agricultural Sciences.

Anderson, E. N. and Sutton, Mark. Q. (2010). Introduction to Cultural Ecology. United Kingdom, AltaMIra press.

Aneesa, Kassam and Gemetchu, Megersa. (1996). "Sticks, Self and Society in Borena Oromo." African Material Culture. Indiana University Press. Pp. 145-166.

Berger, Arthur, A. (2010). The Objects of Affection Semiotics and Consumer Culture. USA, Palgrave Macmillan.

Cutts, Hindi et al. (2010). "The image revealed: Study and Conservation of a mid- nineteenth century Ethiopian church painting." The British Museum Technical Research Bulletin, vol. 4, pp 1-15.

Elisabeth, Biaso. (2009). "Contemporary Ethiopian Painting in Traditional Style Beginning and Change" In proceedings of the 16th International Conference of Ethiopian Studies.

Getinet, Fetene. (2005). "Lake Tana and Its Tourism Potentials." Amhara National Regional State Culture and Tourism Bureau, (unpublished).

Glotfelty and Fromm (ed.) (1996). The Ecocriticism Reader: Landmarks in literary ecology. The University of Georgia press.

Green, Thomas A. (ed). (1997). Folklore An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music and Art. United States of America, California Press.

Ingold, Tim. (2000). The Perceptions of the Environment; Essays on livelihood, dwelling and skill. London and New York, Routledge, Taylor and Francis group.

Martin, Aurora et al. (2011). "The role of secret societies in the conservation of sacred forests in Siera Leone." BOIS ET FORETS DES TROPIQUIES, No. 310 (4), Pp. 44-55.

Mary, Arnoldi (ed.) (1996). African Material Culture. Bloomington and Indianapolis, Indiana University Press.

Milton, Kay. (1996). Environmentalism and Cultural Theory; Exploring the role of anthropology in environmental discourse. London and New York, Routledge, Taylor and Francis group.

Pearce, Susan. (1994). Interpreting Objects and Collections. New York, Routledge.

Teferi, Teklu. (2008). "Forest conservation tradition of the Ethiopian Orthodox Tewahdo Church: The case of West Gojjam zone, North West Ethiopia." Addis Ababa University School of Graduate Studies, Master of Arts in Ethiopian Studies.

Woodward, Ian. (2007). *Understanding Material Culture*. London, SAGE Publications Ltd.